

# ትንሣኤ



በአዲስ አበባ ጉለሌ አዲሱ የደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን



በጐጃም ክፍለ ሐገር ባሕር ዳር አውራጃ በይልማና ዴንሣ ወረዳወነባ ቅዱስ ሚካኤል

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ሥርዓትና ዜና ፡ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ “ትንሣኤ” ተብሎ ተሰይሚል ።»


ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብኅ
ም/ አዘጋጅ መ/ክንፈ
ርግብ ማርቆስ



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ·ቁ· 3137
አዲስ አበባ ፤


# ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ደብዳቤዎች | ፩ |
| (ርእስ አንቀጽ) መድኃኒተ ፈነወ እግዚአብሔር ለሕዝቡ | ፪ |
| ቅዱስ ፓትርያርኩ ቡራኬና መመሪያ ሰጡ | ፬ |
| (ዜና ሊቃውንት) የመምህር ዘካርያስ አምባው የሕይወት ታሪክ በአጭሩ | ፭ |
| የሳባተኛው ዙር ሠልጣኞች ካህናት በገነ ጽ/ቅ· ጊዮርጊስ | ፯ |
| (ዜና ዕረፍት) የአለቃ መንግሥቱ ተጫኔ የሕይወት ታሪክ በአጭሩ | ፰ |
| (የሴቶች ዓምድ) ቤተ ክርስቲያንና ቤተሰብ | ፲ |
| ጾማችሁ እንደግብዞች አይሁን | ፲፩ |
| የአርባ ምንጭ ደብረ መድኃኒት መድኃኔ ዓለም | ፲፫ |
| ጤናችን | ፲፬ |
| ወጣቶች በወላጆች እግር ሲተኩ | ፲፭ |
| ዮም ተወልደ ቤዛ ኩሉ ዓለም | ፲፯ |
| የድሮ ቅርስ ሁልጊዜ አዲስ | ፲፰ |
| ቅንዓት | ፲፱ |
| የማይሞተው አምላክ | ፳፪ |
| በፍቅራችን መካከል ግብዝነት አይኑር | ፳፫ |


## ደብዳቤዎች

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ

አዲስ አበባ ፡

በቅድሚያ መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ከሰላምታዬ ቀጥየ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቀርባለሁ ።

፩ኛ· የሥላሴ ጽላት ያለበት ቤተ ክርስቲየን ሁሉ ቅድስት ሥላሴ እየተባለ ሲጠራ እሰማለሁ ለምን ሥላሴ በሴት አንቀጽ ይጠራሉ ? ለምንስ ቅዱስ ሥላሴ አይባሉም ?

፪ኛ· በዮሐንስ ራዕይ ምዕ ፳፪·፰—፱ ይህንም ያየሁትና የሰማሁት እኔ ዮሐንስ ነኝ በሰማሁትና ባየሁትም ጊዜ ይህን ባሳየኝ በመልአኩ እግር ፊት እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ እርሱም እንዳታደርገው ተጠንቀቅ ከአንተ ጋር ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ ለእግዚአብሐር ስገድ አለኝ ይላል ይህ መልአክ ማነው ? ስሙን ብትጠቅሱልኝ “ደግሞም መልአኩ ለእኔ አትስገድ ያለው ለምንድን ነው ? ለመልአክ ስግደት አይገባም ማለት ነው ? ስግደት የሚገባው ከሆነ ማስረጃ ከብሉይም ሆነ ከሐዲስ ብትጠቅሱልኝ ።

፫ኛ· ለእመቤታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ስግደት አይገባም በተጨማሪም እመቤታችን አታማልድም የሚሉ መናፍቃን አሉና እውነተኛ አማላጅነቷን ከአዋልድ መጽሐፍ ሳይሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ብትሰጡኝ በተጨማሪም ስለጻድቃንና ሰማዕታት አማላጅነት ጠቅሳችሁ ጻፉልኝ ።

፬ኛ· የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲየን ለምን ያሬዳዊ ዜማ ያለው መዝሙር ብቻ ትቀበላለች ሌላውንስ ለምን አትቀበልም ?

፭ኛ· አንድ ካህን መዓርገ ቅስና ከተቀበለ በኋላ ለምእመናን የንስሐ አባት ለመሆን አይችልምን ?

፮ኛ· ሴት ልጅ በተወለደች በ፹ ቀኗ ወንድ ለጅ በተወለደ በ፵ ቀኑ ይጠመቃሉ ለምን በአንድ ቀን አይጠመቁም ?

ዲ· አምሳሉ አበራ ሰሜን ኦሞ አስተዳደር አካባቢ አርባ ምንጭ አውራጃ ባንቴይ ቅ·ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ።

### መልስ

፩ኛ· ቅድስት ሥላሴ ለምን ይባላል ቅድስት የሚለው ቃል ለሴት አንቀጽ የሚቀጸል ሲሆን ለምን ለሥላሴ ተቀጸለ ስላልከው ሥላሴ በሴት አንቀጽም ይጠራሉ ሊቃውንት አባቶቻችን ለዚህ ማብራሪያ ሲሰጡ ሴት ርኅርኅት እንደሆነች ሥላሴም ለፍጥረታቸው ርኅሩኅ ናቸው ፤ በተጨማሪም ሴት ልጅን እንደምታስገኝ ሥላሴም ወላድያነ ዓለም ስለሆኑ በሴት አንቀጽ ይጠራሉ ይላሉ ስለዚህ ነው ቅድስት ሥላሴ የሚባለው ።

፪ኛ· ለዮሐንስ መልአኩ ሲሰግድለት ለእኔ አትስገድልኝ ያለው መልአክ ቅዱስ ሚካኤል መሆኑን አንዳንድ ሊቃውንት ይናገራሉ እኛም የም[illegible]ግባ መልስ ከዚህ የተለ[illegible]ይ ግንም በራዕየ ዮሐንስ ከዲያብሎስ ጋር ተዋጋ የሚለው ቅዱስ ሚካኤልን ነውና ራዕ· ዮሐ· ፲፪·፯ ።

አትስገድልኝ ያለውስ ለምንድን ነው ? ስግደት ለመላእክት የማይገባ ሆኖ ነውን ? ስላልከው ፤ ስግደት በሁለት ይከፈላል አንደኛው የባሕርይ ሲሆን ሁለተኛው የጸጋ ነው የባሕርይ ስግደት የሚሰገደው ለእግዚአብሐር ብቻ ነው የጸጋ ስግደት ግን ለማንኛውም ሰው ተገቢ ነው ። መልአኩ ዮሐንስን ለእኔ አትስገድልኝ ማለቱ ደግ ስለነበር ስለትሕትና ነው እንጂ ለመልአክ መስገድ አይገባም ለማለት አይደለም የጸጋ ስግደት ለፍጡራን እንደሚገባም ለመረዳት ዘፍ ፲፱·፩ የሐ·ሥራ ፲·፳፭ ኢያሱ ፭·፲፫—፲፭ ተመልከት ።

፫ኛ· ለእመቤታችን ስግደት እንደሚገባ ኢሳ ፷፬·፳፫ ፡ መዝ ፻፴፩ ፡ ፲፪ ። የሉቃስ ወንጌል ፩·፵፰ ስለ አማላጅነቷ የዮሐ· ወን· ፪ ፡ ፫—፲ የዮሐ· ወን· ፲፱·፳፮ ተመልከት ስለጻድቃንና ሰማዕታት አማላጅነትም በማቴዎስ ወንጌል ፲ ፡ ፵—፵፪ ብትመለከት ለመረዳት ትችላለህ ።

፬ኛ· የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲየን ለምን ያሬዳዊ ዜማ ብቻ ትቀበላለች ሌላውንስ ለምን አትቀበልም ስለአልከው ከያሬድ የበለጠ ዜማ ባለመኖሩ ነው ። በዚህም ሆነ በዚያ ከግዕዝ ፤ ከዕዝል ከዓራራይ የወጣ ዜማ የለም እነዚህም ሁሉ በያሬድ ዜማ በሚገባ ተቀነባብረው በብዛት ስለተጻፉ እንኳን የሌላውን ዜማ ለማስገባት የራሷን ዜማ ለማዳረስ ጊዜ የላትም ቤተ ክርስቲያናችን ሌላ ዜማ የማትሻው የዜማ ባለጸጋ በመሆኗ ነው ።

፭ኛ· አንድ ካህን መዓርገ ቅስ

(ወደ ገጽ ፱ ዞሯል)



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# “መድኃኒተ ፈነወ እግዚአብሔር ለሕዝቡ” እግዚአብሔር መድኃኒትን ለሕዝቡ ላከ

የታመመ መድኃኒትን ፡ የተራበ ምግብን የተጠማ መጠጥን ፡ የታረዘ ልብስን የደከመ ዕረፍትን ይፈልጋል ፡ በዚህ ዓለም ላይ ለተወሰነ ዘመን እንዲኖር የተፈጠረ ሥጋዊ ደማዊ ፍጡር ሁሉ በዓለመ ሥጋ በሚኖርበት ጊዜ የተለያዩ የኑሮ ሁኔታዎች ይፈራረቁበታል ፡ ከምድራውያን ፍጡራን መካከል ሰው ከፍተኛውን ደረጃ የያዘ መሆኑ የታወቀ ነው ሌሎች ፍጡራን ለአንክሮ ለተዘክሮ የተፈጠሩ ሲሆኑ ሰውና ከፍተኛውን ደረጃ የያዘ መሆኑ የታወቀ ነው ሌሎች ፍጡራን ለአንክሮ ለተዘክሮ የተፈጠሩ ሲሆኑ ሰውና

መላእክት ግን የተፈጠሩት ለውዳሴ ለቀዳሴ መሆናቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዱናል ።

በተለይ ወደ ሰው የኑሮ ሁኔታ ስንመለከት ብዙ የተለያዩ ሁኔታዎችን እናያለን ፡ ለምሳሌ ጤነኛው ይታመማል የታመመው ይድናል የተራበው ይጠግባል የጠገበው ይራባል ፡ የወፈረው ይከሳል የከሳው ይወፍራል ፡ የጠቀረው ይቀላል የቀላው ይጠቁራል የደኸየው ይከብራል ፡ የከበረውም ይደኸያል የተሾመው ይሻራል የተሻረው ይሾማል የተዋረደው ይከብራል የከበረው ይዋረዳል ያዘነው ይደሰታል የተደሰተው ያዝናል በሥልጣኑ በጌትነቱ በክብሩ በገናናነቱ ለዘለዓለም ጸንቶ የሚኖር አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው ነቢዩ ዳዊት ይህንን በመንፈሰ ትንቢት ተመልክቶ “እግዚአብሔርሰ ንጉሥ ውእቱ እምቅድመ ዓለም ወገብረ መድኃኒተ በማዕከለ ምድር” እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር ንጉሥ (ገዥ) ነበር በምድርም መካከል መድኃኒትን አደረገ በማለት ለመንግሥቱ ሽረት በባሕርዩ ኀልፈት እንደሌለበትና በፍዳ በመርገም መድኃኒት

ለጥተው ሲጨነቁ የነበሩትን ሰዎች በቀራንዮ ተሰቅሎ እንደሚያድናቸው ተናግሯል ።

፡ ገዚአብሔር አምላክ ሰውን የፈጠረው በአርዓያውና በምሳሌው እንደሆነ የታወቀ ነው ፈጥሮም ከምድር በላይ ከሰማይ በታች ባሉ ፍጥረታት ሁሉ ሥልጣንን ሰጠው መኖሪያውም ገነት እንድትሆን አደረገ በገነትም ሲያስቀምጠው ከአንዲት ዕንጨት ፍሬ በስተቀር ሁሉንም ፈቀዶለታል ፡ የአንዲቱን የዕንጨት ፍሬ ግን መብላት እንደማይገባው አስጠንቅቆት ነበር ፡ ነገር ግን ዲያብሎስ በሥጋ ከይሲ ተሠውሮ ወደ እርሱ በመቅረብ ለትንካ ተብሎ ከተከለከለው የዕንጨት ፍሬ ቀርጦ ቢበላ በክብር ላይ ክብር በሥልጣን ላይ ሥልጣን እንደሚጨምርለት መከረው በምክረ ከይሲ ተታሎ ለትንካ የተባለውን የዕንጨት ፍሬ ቀጥፎ በላ ፡ ከበላም በኋላ እንኳን ከነበረው ክበርና ሥልጣን በላይ ሊጨመርለት ተሰጥቶት የነበረውን ሥልጣን አጥቶ ከገነት ወጥቶ ተባረረ ፡

ከዚያ በኋላ ኑሮው የደስታ መሆኑ ቀርቶ የኀዘንና የልቅሶ ሆነ ከደረሰበት የኃዘንና የልቅሶ ኑሮ የሚላቀቅበትን መድኃኒት ይሰጠው ዘንድ ወደፈጣሪው አለቀሰ እግዚአብሔር አምላክም ኀዘኑንና ልቅሶውን ሰምቶ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ተሰቅሎ ሞቶ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ እንደሚያድነው ተስፋ ሰጠው ።

ነገር ግን የተሰጠው ተስፋ የሚፈጸመው በቅርብ ጊዜ አልነበረም እስከ ፭ሺህ፭፻ ዘመን ድረስ የሚዘገይ ነበር ምንም ከዘመኑ ለመድረስ ተስፋ ባይኖረውም አዳም በተሰጠው የተስፋ ቃል መጽናናቱ አልቀረም ፡ዚህ ዓለም ላይ የኖረው ፱፻፴ ዓመት ቢሆንም የተሰጠውን ተስፋ ለልጆቹ በሚገባ አስጠንቶ አልፎአል ። ይህ የተሰጠው ቃለ ተስፋ ቃል ለቃል እየተነገረ እስከ ሙሴ ደርሷል ከሙሴ ዘመን ወዲህ በመጽሐፍ ተጽፎ የሚነበብ ሆኗል ሙሴ በደብረ ኮሬብ በጎቹን አሠማርቶ ሲጠብቅ ነበልባል ከሐመልማል ጋር ተዋሕዶ አይቶ ቀረብ ብሎ ቢመለከተው ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥለው ሐመልማሉ ነበልባሉን ሳያጠቁረው አገኝቶታል ። ይህም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ከፍዳና ከመርገም ለማዳን ከቅድስት ድንግል ማርያም የሚወለድ መሆኑን የሚያስረዳ ነበር ከሙሴም ቀጥለው በየዘመኑ የተነሡ ነቢያት ሁሉ የሰው ልጆች ከኃጢአት በሽታ የሚድኑበት ጊዜ መቃረቡን እየተነበዩ አልፈዋል ፡ ዳዊት መድኃኒተ ፈነወ እንዚአብሔር ለሕዝቡ እግዚአብሔር መድኃኒት ይሆን ዘንድ ጌታችን መድኃኒታችን

ኢየሱስ ክርስቶስን ውረድ ፡ ተወለድ ፡ ተሰቀል ፡ ሙት ፡ ብሎ ወደዚህ ዓለም ላከው ሲል ቀደም አድርጎ ትንቢት ተናግሮ ነበር የተነገረው ትንቢት የተቆጠረው ሱባኤ ወደፍጻሜ ሲደርስ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ተወለደና ቀስ በቀስ አደገ በዚህ ዓለም በሥጋ ሰብእ በኖረበት ዘመንም አንዳንድ ጊዜ የአዳኝነቱን ሥራ ከመሥራት አልቦዘነም ።

እንዲሁም ሰው እንደመሆኑ መጠን መንገድ በመሄድ ደክሞአል ። ይህንንም ወንጌላዊው ዮሐንስ ሲገልጽ “ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ በመሄድ ደክሞ በውኃ ጉድጓድ አጠገብ ተቀመጠ ጊዜውም ስድስተ ሰዓት ያህል ነበረ” የዮሐ. ወን. ፬ ፡ ፮ ከኃጢአት በስተቀር የሰው ልጆች የሚቀበሉትን ችግር ሁሉ እየተቀበለ ካደገ በኋላ በሰላሳ ዘመኑ በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ እንደተጠመቀ ሳይውል ሳያድር ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ሂዷል ። በዚያም ፵ መዓልትና ፵ ሌሊት ጾመ መዋዕለ ጾሙን ሲፈጽም ሰይጣን በስስት በትዕቢት በፍቅረ ንዋይ ተፈታተነው ፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በስስት የመጣውን በትዕግሥት በትዕቢት የመጣውን በትሕትና በፍቅረ ንዋይ የመጣውን ሰይጣን በፀሊአ ንዋይ ድል በማድረግ አባርሮታል ። ማቴ. ፬.፩—፲፩ ።

ከዚያ በኋላ ለስብከተ ወንጌል የሚፋጠኑ ደቀ መዛሙርቱን እየመረጠ ከማስተማሩ ጋር በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱን ገለጸ የዕለተ ሬሣ ወለተ ኢይሌሮስን ፡ የአራት ቀን ሬሣ አልዓዛርን አሥነሣ ፴፰ ዓመት ሙሉ በአልጋ ቁራኛ በደዌ ዳኛ ተይዞ ይሰቃይ የነበረውን በሽተኛ አዳነ ከእናቱ ማኅፀን ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው ዓይን አበራ እንደ የብስ በባሕር ላይ ተጓዘ እነዚህ ሁሉ የአዳኝነቱን ተግባር ከሚገልጹት ጥቂቶቹ ነበሩ ።

ይሁን እንጂ የሰው ልጆች ሁሉ በጠቀላላ ፍጹም ድኅነትን ለ...ገኘት የሚችሉት በቀራንዮ አደባባይ ተሰቅሎ በሚሠዋው ሥጋው በሚያፈሰው ደሙ መሆኑ ቀደም ብሎ ተነግሮ ስለነበር ይህንን የድኅነት ተስፋ ለመፈጸም ሲል መጋቢት ፳፯ ቀን የዛሬ ፲፱፻፶፯ ዓ/ም ተሰቅሎ ከአዳም ጀምሮ እስከ ዕለተ ስቅለት የነበሩትን ነፍሳት ከሲኦል አወጣቸው ።

ሐዋርያው ጳውሎስ “ተሣሃለነ በሞተ ወልዱ” በልጁ ሞት አዳነን ብሎ እንደገለጸው አዳኝነቱን አምኖ የተቀበለ ሁሉ በክርስቶስ ሞት ከኃጢአት ቁራኝነት የተላቀቀ ስለሆነ እንግዲህ ወዲህ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የለበትም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው ለመላው ዓለም ነው እንጂ ለተለዩ ሰዎች አይደለም ለመዳን የሚፈልግ ደግሞ አዳኝነቱን አምኖ መቀበል አለበት ፡ በሽተኛ መድኃኒቱ ወደሚገኝበት መሄድ አለበት እንጂ መድኃኒቱ ወደበሽተኛው እንደማይመጣ ሁላችንም እናውቃለን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የኃጢአት በሽተኞች የሆነው እኛ ወደ አለንበት በሥጋ በመምጣት አድኖናል ።

አዲስ ጨርቅ ምንም በጥንቃቄ ቢይዙት ማደፉ አይቀርም ቀጥሎም ማለቁ የማይቀር ጉዳይ ነው ሰውም ሲወለድ በንጽሐ ጠባይዕ መሆኑ ቢታወቅም ያለ ኃጢአትና ያለበደል ለመኖር አይችልም ሰውነቱ በኃጢአት ያረጃል ያረጀው ሰውነቱም ለመታደስ የሚችለው በንስሐ በጸሎት በጾም በስግደትና በመሳሰሉትም ሥነ ምግባራት ነው ።

ሁላችንም ከኃጢአት ንጹሐን አይደለንም በሐልዮ በገቢር በምንፈጽመው ክፉ ሥራ እግዚአብሔር አምላካችን እንበድላለን ሐዋርያው ዮሐንስ “ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን እውነትም በእኛ ውስጥ የለም በኃጢአታችን ባንናዘዝ ኃጢአትን አላደረግንም ብንል እግዚአብሔርን ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም” ብሏል ፩ኛ. ዮሐ.፩.፰—፲ ።

የባሕርይ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደዚህ ዓለም ልኮ በእግረ አጋንንት ተጠቅጥቀው በመንጸፈ ደይን ወድቀው የነበሩትን የአዳም ልጆች ሁሉ ነፃ ያወጣ አምላክ በሰላም ዕጦት በበሽታ በረኃብ በድንቁርና ተይዞ የሚጨነቀውን ዓለም በቸርነቱ ይጉበኝልን ዘንድ የድኅነት ባለቤት የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ዘወትር እንለምነዋለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ፓትርያርኩ ቡራኬና መመሪያ ሰጡ

ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ በጂቡቲ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምሥራቀ ፀሐይ ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን መታሰቢያ ድርጅት አባላት ቡራኬና መመሪያ ሰጥተዋል ።

ቅዱስነታቸው ይህን ቡራኬና መመሪያ የሰጡት ታህሣስ ፲፱ ቀን



ቅዱስነታቸው ለጅቡቲም ፀሐይ ቅዱስ ገብርኤል ተሳላሚዎች መመሪያና ቡራኬ ሲሰጡ

፲፱፻፹፫ ዓ.ም በጂቡቲ የቅዱስ ገብርኤልን በዓል ለማክበር በስብከተ ወንጌል አዳራሽ ለተሰበሰቡት ምእመናን ነው

ቅዱስነታቸው በዚሁ ዕለት ለምእመናኑ በሰጡት ቃለምእዳን ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ተለያይተው አልኖሩም ሊኖሩም አይችሉም ፣ ለምሳሌ ፣

ምእመናን ቤተ ክርስቲያንን እናታችን ብለው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሊያደርጉ የሚገባቸውን ሲያደርጉ ኖረዋል ፣ አሁንም እያደረጉ ናቸው ይህ የናንተ እንቅስቃሴም አንዱ ማስረጃ ነው ፣

ቤተ ክርስቲያንም ምእመናንን ልጆቼ ብላ በዚህ ዓለም ሲኖሩ በሰላምና በጤና እየሠሩ እንዲኖሩ የተወለዱ ልጆች ተምረው ለቁምነገር በቅተው የሀገርና የቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪዎች እንዲሆኑ ስትጸልይ ኖራለች አሁንም ትጸልያለች ።

ይህም የጸሎት ውጤት ዓለም በጠቅላላ ሰላም ሆኖ የሰው ልጅ ከዕለት ወደ ዕለት የዕለት ኑሮውን በሰላም እየመራ ከአንዱ ሀገር ወደ ሌላው ሀገር ከአንዱም ዓለም ወደ ሌላው ዓለም ያለችግር እንዲሸጋገር አስችሏል ።

ይህም ከኢትዮጵያ ወደ ጅቡቲ ለመጓዝ ትችሉ ዘንድ በዚህ አዳራሽ ተሰብስባችሁ ጸሎትና ቡራኬ ለመቀበል የፈለጋችሁት ደስ የሚያሰኝ ነው ።

በጅቡቲ የተቋቋመው የምሥራቀ ፀሐይ ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ጥረት ሲሆን ዛሬ የቅዱስ ገብርኤልን ዓመታዊ በዓል ምክንያት በማድረግ ይህን ያህል ሕዝብ ወደ ጅቡቲ ለመጓዝ በመቻሉ ቤተ ክርስቲያናችንን ያኮራታል ሊቀ ጳጳሱንም ያስመሰግናቸዋል።

ይህ በጂቡቲ የተቋቋመው የቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም አምሳል የሚታይ ነው የኢየሩሳሌምን ታሪክ አስታውሱ ፣ እንዲህም የምንለው ብዙ ምክንያት ስለሚኖረው ነው ስለሆነም በዚህ ቦታ ተገኝቶ በዓሉን አክብሮ መመለስ ፀጋና ክብርን የሚያጐናጽፍ በመሆኑ መንፈሳዊ ዓላማችሁን አጠናክራችሁ መገኘት ይኖርባችኋል ብለዋል ።

ቅዱስነታቸው ቀጥለው ሲናገሩ በመንፈሳዊ ዓላማው ጠንክሮ የሚገኝ ሰው ከእግዚአብሔር ኃይልና እርዳታ ይሰጠዋል ፣ የመልአኩ ቅ/ገብርኤል ተራዳኢነትም አይለየውም በዘመነ ነቢያት ጠንካራ እምነት የነበራቸው ሰዎች ነበሩ እኒህም ሰዎች በአንድ ወቅት ከፈጣሪያቸው የሚለያይ ምክንያት ገጠማቸው ሳያመነቱና ሳያወላውሉ በጠንካራ እምነት የምናመልከው አምላካችን ከሚነደው እሳት ያድነናል ብለው ከዓላማቸው ፈቀቅ ሳይሉ ወደ ፊት ቀጠሉ ያ የሚነድ እሳትም ተዘጋጀ ወደ እሳቱም ተጣሉ እግዚአብሔር አምላክም መልአኩን ልኮ አዳናቸው ዳንኤል ፫፥ ፩—፳ ተመልከቱት ይህ በዓል በዚህ ምክንያት የሚከበር ስለሆነ እናንተም በዚህ ማኅበር አምናችሁና ማኅበራችን ብላችሁ ልታስቡለት ይገባችኋል ብለዋል ፣

ቅዱስነታቸው ስለ ባሕል ልብስ ጠቃሚነት አንስተው ሲናገሩ የባሕል ልብስ አስተማሪ ነው በመሆኑም በበዓሉ ላይ የባሕል ልብሳችሁን ለብሳችሁ ብትገኙ



የምድረ ጅቡቲ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ

በዓሉን ከማድመቁም በላይ ኢትዮጵያን የሚያስተዋውቅ ይሆናል።

ስለዚህ የባሕል ልብሳችሁን በመልበስ በዓሉን ለማክበር ጥረት አድርጉ ብለዋል ።

የቅዱስነታቸው መመሪያ ቀጥሎ ይህ በጂቡቲ ቤተ ክርስቲያን ስም የተሰየመው መታሰቢያ ድርጅት በዚህ ብቻ የሚወሰን አይሆንም በሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤልያስ ጥረት በተቋቋሙት፣ በኬንያ ፣ በጀርመንና በግሪክ በሱዊድንም ድርጅቱ ተጠናክሮ የሚቀጥል ስለሆነ የአንድ ጊዜ አባል ሳትሆኑ ቋሚ አባል በመሆን ጠንክራችሁእንድትገኙ ያስፈልጋል ብለዋል ፣

ከዚህ ቀደም ሲል የመታሰቢያ ድርጅቱ ም/ሊቀ መንበር አቶ ጌራሚካኤል ብርሃኑ ስለመታሰቢያ ድርጅቱ ዓላማና አቋም እንዲሁም በዚህ ጉዞ 189 አባላትና 7 ካህናት ታህሣሥ 19 ቀን 1983 ዓ.ም በጂቡቲ ተገኝተው በዓሉን አክብረው ለመመለስ የተዘጋጁ መሆናቸውን ለቅዱስነታቸው አስረድተው አባላቱ በሰላም ሔደው በደስታ እንዲመለሱ ቡራኬና መመሪያ እንዲሰጡልን በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ ብለዋል ።

ከዚህ በኋላ ቅዱስነታቸው ቡራኬና ጸሎት ሰጥተው ምእመናኑን አሰናብተዋል ።

የዜናው አቅራቢ በለጠ አበበ

## ዜና ሊቃውንት

# የመምህር ዘካርያስ አምባው የሕይወት ታሪክ በአጭሩ

መምህር ዘካርየስ አምባው በጎንደር ሀ/ስብከት በጋይንት አውራጃ በስማዳ ወረዳ ስዴ ሙጃ በምትገኘው ንብ አዝላ ማርያም ከተባለችው ደብር ከአባታቸው አቶ አምባው ከእናታቸው ወ/ሮ አንጓቸ ንጉሤ በ፲፱፻፳፮ ዓ/ም ጥቅምት ፴ ቀን ተወለዱ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ በተወለዱበት ደብር ከአባታቸው ወንድም ባሕታዊ ፀጋዬ ግዛው ፊደል ቆጥረው ንባብና ዳዊት ተማሩ ።

ከዚያም በኋላ ወደ ወሎ ክፍለ ሀገር ሄደው ተድባበ ማርያም ከነበሩት መምህር ገብረ መድኅን ፀዋትወ ዜማን በሚገባ አጠናቀው ተምረው ወደ ሀገራቸው ተመለሱ ቀጥለውም በስማዳ ወረዳ ከምትገኘው ደብረ ዕንቍ ማርያም እጅግ ዝነኛና ታዋቂ ከነበሩት መምህር ጌጡ ተሰማ

፩ኛ· ቅኔውን ከነ አገባቡ ዕርባ ቅምሩን ከእነዓዋጁ ተማሩ

፪ኛ· የዳዊት ትርጓሜን

፫ኛ· የአርባዕቱ ነገሥት ትርጓሜን

፬ኛ· የውዳሴ ማርያምና የቅዳሴ ማርያምን ትርጓሜ

፭ኛ· ባሕረ አሳብን በሚገባ አጠናቀው ተምረው እንዲያስተምሩ ለዕውቀታቸውም ምስክር የሚሆን ከመምህራቸው ። መምህር ጌጡ ተሰማ የምሥክር ወረቀት ተቀብለዋል ።

ከዚያም ወደ ሸዋ ክፍለ ሀገር መጥተው ሰላሌ አውራጃ ሥሬ መድኃኔ ዓለም ከነበሩት መምህር ጥበቡ ገሜ ከሚባሉት ታዋቂና ዝነኛ ሊቅ የአዲስ ኪዳን ትርጓሜን ተምረዋል ። በዚያን ዘመን መምህራቸው ጌጡ ተሰማ የፈረሰችውን ደብረ ዕንቍ ማርያምን ለማሠራት አስጀምረው ስለነበር ከጉባኤው ጋር እንዳያስቸግራቸው በማሰብ መምህራቸውን ለመርዳት ሲሉ ተመልሰው ደብረ ዕንቍ ገብተዋል ከዚያም ግሥ በመግሠሥ ቅኔ በመዝረፍና እያስቆጠሩ በማስነገር መምህራቸውን ሲረዱና ሲያገለግሉ ለአንድ ዓመት ቆይተው ከመምህራቸው





www.ethiopianorthodox.org

በረከትን ተቀብለዋል ።

መምህር ዘካርያስ አምባው በተማሩት ዕውቀት ሳይወሰኑ ሌላም ዕውቀት ለመቅሰም ፍላጐት ስለነበራቸው መምህር ጌጡ የአደራ ደብዳቤ ጽፈውላቸው በደብረ ታቦር አውራጃ ፋርጣ ወረዳ በምትገኘው እንዘና ማርያም ደብር ከነበሩት መምህር ሲራክ ከተባሉት የድጓ መምህር ገብተው በአንድ ጐን ቅኔ እያስተማሩ የዜማ ትምህርታቸውን አጠናክረዋል ።

ከዚያም በኋላ ወደ መምህር ጌጡ ተመልሰው መጥተው በጉባኤያቸው እንዲተኩ ስለላኩባቸው መምህር ዘካርያስ እንደመጡ መምህራቸው እርሳቸውን ተክተው ወደግሸን ማርያም ሂደዋል ። በመምህር ጌጡና በመምህር ዘካርያስ መካከል የነበረው ፍቅር ከባስልዮስና ከኤፍሬም ከኤልያስና ከኤልሳዕ ተለይቶ የማይታይ ነበር ይኸውም ይታወቅ ዘንድ መርቀው ከባና ቀሚስ ሙሉ ልብስ ሸልመው ወደትውልድ ሀገራቸው ተመልሰው ሂደው ወንበር ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው እንዲያስተምሩ በ፲፱፻፵፩ ዓ/ም ጥር ፺ ቀን በጸሎት ሸኝተዋቸዋል ።

መምህር ዘካርያስ ወደ ትውልድ ሀገራቸው ንብ አዝላ ማርያም አጠገብ በሚገኘው ዝሆን ወጊ በዓለ እግዚአብሔር በተባለው ደብር ጉባኤ ዘርግተው ፴ ዓመት በንቃትና በትጋት አስተምረው ለቁጥር የሚያዳግቱ ደቀ መዛሙርትን አስተምረው ለቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል ቅኔ እየተቀኙና እያወቁ የሄዱትን ሳንቆጥር በማስተማር ላይ ከሚገኙት ጥቂቶቹን ለማስረጃ ያህል እንጠቅሳለን ።

፩ኛ. መሪጌታ ኃይለ ማርያም ሸዋ

፪ኛ. መሪጌታ ናሁሠናይ ገብረ ሥላሴ ዋድላ መቄት

፫ኛ. መሪጌታ መክብብ ገብረ ሐና ሸዋ



መምህር ዘካርያስ ከጥቂቶች ተማሮቻቸው ጋር

፬ኛ. አባ ሐረገ ወይን ቸሩ ሳይንት

፭ኛ. መሪጌታ ቀጸላ ወርቅ

፮ኛ. መሪጌታ የማነ ብርሃን

፯ኛ. መሪጌታ ቀለመወርቅ ወዘተ ናቸው ። መሪጌታ ዘካርያስ አምባው የቃለ እግዚአብሔር ፍቅር በልባቸው የተጻፈ በመሆኑ ከእርሳቸው ቅኔ ለመማር ከሚመጡት ሊቃውንት ዝማሬና መዋሥዕት አቋቋም ተምረው አውቀዋል።

መምህር ዘካርያስ አምባው "ብዝኁ ወተባዝኁ መምልዕዋ ለምድር" ባለው ቃል መሠረት <u>እናቴ ወዳ</u> ንጉሤን በተክሊልና በቁርባን አግብተው ሦስት ወንዶችን ሦስት ሴቶችን በድምሩ ስድስት ልጆችን ወልደዋል በ፲፱፻፵፱ ዓ/ም ከብፁዕ አቡነ ሚካኤል የዲቁና መዓርግን በ፲፱፻፷፩ ዓ/ም ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ የቅስና መዓርግን ተቀብለዋል ።

መምህር ዘካርያስ ከ፲፱፻፶፩ ዓ/ም ጀምሮ ጉባኤ አስፍተው ወንበር ዘርግተው በማስተማር በተጨማሪ ሌሊት በሰዓታት ቀን በማኅሌት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ቤተ ክርስቲያንን አገልግለዋል ከ፲፱፻፶፩—፲፱፻፸፰ ዓ/ም በትሩፋት ያለ ደመወዝ ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ ቆይተዋል ።

አሁን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የጎንደር ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ በነበሩ



# የሰባተኛው ዙር ሰልጣኞች ካህናት በገነተ ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ

በሀገራችን በኢትዮጵያ አህጉረ ስብከት ቁጥራቸው ከ፺ በላይ የሆኑ የካህናት ማሠልጠኛዎች መኖራቸው የታወቀ ነው ከ፪፻፸፫ ሺህ በላይ ለሚገመቱ ካህናት አሁን የተቋቋሙት ማሠልጠኛዎች ብቁ ናቸው ባይባሉም የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል እንደሚባለው አጀማመራቸውና አያያዛቸው እጅግ በጣም የሚያስደስት ነው ።


ቋመው የካህናት ማሠልጠኛ በአጭሩ እንመልከት ማሠልጠኛው የተከፈተው በጥቅምት ወር ፲፱፻፸፭ ዓ·ም ሲሆን እስከ ዛሬ ድረስ ፫፻፲፪ ካህናትን አሠልጥኖ በተገቢው ሥራ እንዲመደቡ ከማድረጉም ሌላ ሌሎችም እየሠለጠኑ ናቸው ከሚሠለጥኑት መካከልም የተለያዩ ስጦታዎች ያሏቸው ስለሚገኙ ያከህናቱን አቅምና ችሎታ ስጦታና ዝንባሌ አበ

በት ጊዜ ፳፭ ብር ድጐማ መድበውላቸዋል ። በ፲፱፻፸፱ ዓ/ም በስማዳ ወረዳ ቤተ ክህነት አዳሪ መንፈሳዊ ት/ቤት ሲከፈት በወር ፳ ብር እያገኙ ቅኔና መጽሐፍ እንዲያስተምሩ ተመድበዋል ።

የመንፈስ ቅዱስ አባታቸው መምህር ጌጡ ተሰማ ቀደም ብለው ወደ አዲስ አበባ መጥተው ስለነበር መጥተህ ጠይቀኝ ብለው ስለላኩባቸው ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከአባታቸው መምህር ጌጡ ጋር ተገናኝተው ከእርሳቸው ካባና ቀሚስ ተሸልመው ወደ ቦታቸው ተመለሱና የተመደቡበትን ሥራ ቀጠሉ ።

ይህ በዚህ እንዳለ አባታቸው መምህር ጌጡ ተሰማ በ፲፱፻፸፩ ዓ/ም መሞታቸውን ስለሰሙ ወደ አዲስ አበባ መጥተው እስከ ፴ ቀናቸው በኃዘን በጸሎት ሰንብተው እመለሳለሁ ሲሉ የማኅደረ ስብሐት ማኅበረ ካህናት በአባታችን በመምህር ጌጡ ተሰማ እግር ተተክተው ያስተምሩልን ሲሉ የድጋፍ ደብዳቤ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ጻፉ ቅዱስነታቸውም ፈቅደውላቸው አሁን አዲስ አበባ ከተማ በማኅደረ ስብሐት ልደታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ወንበር ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው በማስተማር ላይ ይገኛሉ ።

የዜናው አቅራቢ ቀ·ሊ·ኅ ልሣኑ በዛብኅ



የ፯ኛ ዙር ሠልጣኞች ካህናት በገነተ ጽጌ ቅ/ጊዮርጊስ

ከእየማሠልጠኛዎቹ ተምረው የሚወጡት ካህናት ሁለገብ ትምህርት ቀስመው ስለሚወጡ በማንኛውም የሥራ ቦታ እየተመደቡ መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን በማበርከት ላይ ይገኛሉ የሠለጠኑ ካህናት በሰበካ ጉባኤ አደራጅነት በሰንበት ት/ቤት በልማትና በመሳሰሉትም ማኅበራዊ ኑሮ እየገቡ ስለሚያገለግሉ ቤተ ክርስቲያንን እያስመሰገኑ ናቸው ይህንንም ከማሠልጠኞች በየጊዜው ከሚቀርበው ሪፖርት ለመረዳት ይቻላል።

የሌሎችን ማሠልጠኛዎች ይዞታ ለሌላ ጊዜ አቆይተን ከላይ በተጠቀሰው በገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ስለተቋ

ጥሮ አውቆ በየችሎታቸው መድቦ ለማሠራት ማሠልጠኛው ፍቱን መድኃኒት ነው የ፯ኛው ዙር ሠልጣኞች ካህናት ጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ/ም ጉባኤ አድርገው ከሠለጠኑ በኋላ ስለሚያከናውኑአቸው ሥራዎች ተወያይተዋል ። በጉባኤውም ላይ ከአንዳንዱ ካህናት ቅኔዎችና የአማርኛ ግጥሞች ተነግረው ነበር በጊዜው ቀርበው የተነበቡት ግጥሞች በርከት ያሉ ስለሆኑ ሁሉንም ለአንባብያን ለማቅረብ ባንችልም ጥቂቶቹን ቀጥለን አቅርበናቸዋል ።

<u>ጉባኤ ቃና ከሊቀ ጠ/ምህሩ ወ/ገብርኤል ቀጨኔ</u>

እፎኑመ ቆመት አእምሮ ከህናት ጣዕዋ



www.ethiopianorthodox.org

በሠላስ አውራህ አምጣነ ተወልደት ነዋ
<u>ትርጓሜ</u> የካህናት ዕውቀት እንቦሳ
እንደምን ብላ ቆመች
በተፀነሰች በሦስት ወሯ ተወልዳለችና

## <u>የአማርኛ ግጥም</u>

<u>ከመ/ጥዑመ ልሣን ይዘን ጋው</u>

### <u>ስለ ሰላም</u>

እስኪ በስመአብ ብዬ ልጀምር ሰላምታ
ለተቀመጥንበት ላለንበት ቦታ
ሰላምን እንመሥርት በየደረስንበት
ሰላም ስለሆነ የሰው ልጆች ሕይወት
ሰላም ያስፈልጋል ለፍጥረቱ ሁሉ
እስኪ ሁላችሁም ሰላም ሰላም በሉ
ሰላም ሰላም ሲባል ሰላም ይሰጠናል
ከሰላም የሚበልጥ አሁን ምን ይገኛል ።
ካህናት ተነሡ አስተምሩ ሕዝቡን
ጥላቻ እንዲወገድ ባሁኑ ዘመን ፤
የሰላም ባለቤት ሰላም እንዲሰጠን
እንጸልይ ወደ አምላክ ባንድነት ተነሥተን
ሰላሜን በሙሉ እኔ ሰጠኋችሁ
እንግዲህ ስበኩ ሳትሰንፉ ተግታችሁ
ሰላምን የሚወድ ቸሩ ፈጣሪያችን
ከሰላም ገበያ ሁልጊዜ እንዳይለን
በጢትም በማታም እንለምነዋልን
ሰላም ሰፍኖ ይኑር በመካከላችን
ሰላም በሀገራችን ይንገሥ ለዘለዓለም
ይህ ነው ምኞታችን በጢትም በማታም

# ዜና ዕረፍት

## የአለቃ መንግሥቱ ተጫኔ አጭር የሕይወት ታሪክ

አለቃ መንግሥቱ ተጫኔ ከአባታቸው ከአቶ ተጫኔ ከእናታቸው ከወ/ሮ ዋጋዬ ካሣዬ የካቲት 2 ቀን ፲፱፻፩ ዓ/ም በሰላሌ አውራጃ በግራር ጀራርሶ ወረዳ ልዩ ስሙ ሽንኩርት ቅዱስ ሚካኤል በተባለው ደብር ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደ ደረሰ ስመ ጥር ከሆኑት መምህር ከአለቃ ጎሩይ በሽንኩርት ሚካኤል ከንባብ እስከ ጾመ ድጓና ምዕራፍ ተምረው ከብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ግብጻዊ ዲቁና ተቀብለዋል ። በ፲፱፻፲፯ ዓ/ም በወሎ ክፍለ ሀገር ወደሚገኘው ወደ ተንታ ሚካኤል ሄደው ከታላቁ የቅኔ መምህር ከአለቃ መርዓዊ ቅኔ ከእነ አገባቡ ተምረዋል ፤ እንዲሁም የሐዲሳትን ትርጓሜ የውዳሴ ማርያምንና የቅዳሴ ማርያምን የትምህርተ ኅቡዓትን ትርጓሜ በሚገባ ተምረዋል ።

አለቃ መንግሥቱ ሕይወታቸውን ለመንፈሳዊ ዕውቀት አዘጋጅተውት ስለነበር ከወሎ ክፍለ ሀገር ከላይ የተጠቀሱትን መንፈሳውያን ዕውቀቶች ከገበዩ በኋላ" እስመ ጸጊበ ትምህርት ኃጢአት ውእቱ ፤ ትምህርት ጠገብሁ ማለት ኃጢአት ነውና" እንደተባለው ትምህርት በቃኝ ሳይሉ በቀጥታ ወደ በጌምድር (ጎንደር) ሄደው በዙር አምባ አረጋዊ ከመምህር ኮከብ ዝማሬና መዋሥዕት ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ። እንደገናም ወደ ወሎ ክ/ሀገር ተመልሰው በሰቆጣ አውራጃ ከአለቃ ዓለሙ (ሰቆጤ ዓለሙ) አቋቋም ተመርው በመምህርነት ተመርቀዋል ። ወደ ቤተ ልሔምም በመሄድ ድጓ ከሊቀ ካህናት መርሻ ገ/እግዚአብሔር አስመስክረዋል ።

በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም አለቃ መንግሥቱ ፫ ያህል ደቀ መዛሙርትን አስከትለው ወደ ትውልድ ሀገራቸው ተመለሱ ። በዚያው በትውልድ ቦታቸው የአቋቋም የዝማሬና መዋሥዕት ወንበረ ዘርግተው ማስተማር ጀመሩ ።

በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ጠላት ሀገራችንን በወረረ ጊዜ አለቃ መንግሥቱ በሰፊው የዘረጉት ወንበር ታጠፈ፣ ደቀ መዛሙርቶቻቸው ወደ እየመጡበት ተበተኑ ። በዚህ ጊዜ አለቃ መንግሥቱ በሰላሌ አውራጃ አራጅሩ ጀሉስ ተክለ ሃይማኖት በተባለው አባታቸው ቦታ በመምህርነት እያገለገሉ ፣ በጠላት ኃይል ብዙ ግፍ ይፈጽበት የነበረውን ወገን እያጽናኑ እያስተማሩና እየ



አለቃ መንግሥቱ ተጫኔ እኒህ ነበሩ

መከራ የወረራውን ዘመን አሳልፈዋል ።

አለቃ መንግሥቱ ተጫኔ በ፲፱፻፴፩ ዓ/ም ወ/ሮ ምዕራፈ ሥላሴ ኃይለ ማርያምን በሥርዐተ ተክሊል አግብተው ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወልደዋል ።

የአለቃ መንግሥቱ ሙያ ዜማ ቅኔ አቋቋምና ትርጓሜ መጻሕፍት ብቻ ሳይሆን የቁም ጽሕፈት ባለሙያም ነበሩ ። በቀድሞው መንግሥት ጊዜ ጥንታውያን መጻሕፍት በግዕዝና በአማርኛ በቁም ጽሕፈት እየተጻፉ እንዲበዙ በታቀደ ጊዜ የግዕዝና የቁም ጽሕፈት ችሎታ ያላቸው ሊቃውንት ሲፈለጉ አለቃ መንግሥቱም የዚህ ባለሙያ ሆነው ስለተገኙ በዚህ ሥራ ተመድበው ብዙ መጻሕፍትን ጽፈዋል ። ከጻፏቸው መጻሕፍትም ፣

፩) ሐዲስ ኪዳን ፣
፪) መጻሕፍተ መነኮሳት
፫) መጽሐፈ ሐዊ
፬) ፍትሐ መንፈሳዊና ሥጋዊ (ፍትሐ ነገሥት) ጥቂቶቹ ናቸው ።

በመጨረሻም ሙያቸውና የረጅም ጊዜ አገልግሎታቸው ታይቶ የሽንኩርት ሚካኤል ደብር አስተደዳሪነት ተሰጥቶአቸው በጡረታ እስከተገለሉ ድረስ በቅንነትና በታማኝነት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ ኖረዋል ።

ከፀሐይ በታች ሕይወት ያለው ፍጡር ሁሉ በሞት ጥላ መጋረጃ አይቀርምና አለቃ መንግሥቱ በዚህ ዓለም የተፈቀደላቸው ጊዜ ሲፈጸም ድንገት ባደረባቸው ሕመም ሐኪም ቤት ገብተው ብጥቂት ቀናት በሕክምና ሲረዱ ከቆዩ በኋላ መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም በተወለዱ በ፹፩ ዓመት ዕድሜያቸው ዐርፈዋል ።

አስከሬናቸው በቀጨኔ ደብረ ሰላም ምድኃኔ ዓለም በወንድማቸው ቤት ዐርፎ ። የቀጨኔ ካህናት ጸሎተ ፍትሐት ሲያደርሱ አድረዋል ። በማግሥቱም ወደ ደብረ ሊባኖስ ተጉዞ ቀደም ሲል በተዘጋጀላቸው መካነ መቃብር አስከሬናቸው ዐርፏል ።

ብንኖርም ብንሞትም ለእግዚአብሔር ነን" በማለት ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ማንም ሰው በዚህ ዓለም መፈጠሩ እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው ። መሞቱም የእግዚአብሔርን ክብር ለመውረስ ነው ። በዚህ መሠረት አለቃ መንግሥቱ ተጫኔ የቤተ ክርስቲያን ቁልፍ የሆኑትን ፀዋትወ ዜማ አቋቋምና የመጻሕፍትን ትርጓሜ ለደቀ መዛሙርቶቻቸው በማስተማር ምእመናንን በመምከርና ቤተ ክርስቲያን የምትገለገልባቸውን መንፈሳውያን መጻሕፍትን በቁም ጽሕፈት በመጻፍ እግዚአብሔርንም ሰውንም አገልግለዋል ። ከብዙ የአገልግሎት ዘመን በኋላም እግዚአብሔር በክብር ጠርቶአቸዋል" ለእኒህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን አባት ለነፍሳቸው ዕረፍት መንግሥተ ሰማያትን ለቤተ ሰቦቻቸው መጽናናትን ይሰጣቸው ዘንድ ወደ ፈጣሪ እንጸልያለን ።

የዜናው አቅራቢ
ልሳኑ ተጨነ

<u>ከመ ክፍለ ማርያም ጌትነት</u>

### <u>ስለ ሀገር ሰላም</u>

ስለ ኢትዮጵያ ስለ እናት ሀገሬ
እስኪ ትንሽ ስሙኝ አፌን ልከፈት ዛሬ
አባቶች ካህናት ወንድሞች ሁላችን
ሰላም ለተጠማች እናት ሀገራችን
ምንድን ነው ትርጉሙ ዝም ማለታችን ፤
ሰላም ሰላም እያልን እንጸልይ ሁላችን
በደንብ እንዲሰማን ቸሩ ፈጣሪያችን
ሰላም ጠቃሚ ነው ለሁሉም ነገር
ኃዘንን ለመርሳት ደግሞም ለመከበር ፣
ጭንጫውን ልባችንን አለስልሰው አምላክ
ሰላም ሲዘራበት እንዲበቅል በመልክ
የሚስተካከለው የልብ ሚዛኑ
ውጤቱ የሚያምረው ዕቅዱ ውጥኑ
ሰላም ሲሰፍን ነው በየማዕዘኑ ።

የዜናው አቅራቢ
ቀሲስ ልሣኑ በዛብኅ



## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፩ የዞረ)

ናን ከተቀበለ በኋላ የንስሐ ልጅ ቢይዝ የሚከለከለው አንዳች ነገር የለም ሊይዝ ይችላል ። ፵ኛ አዳም በተፈጠረ በ፵ ቀኑ ልጅነትን ከሥላሴ አግኝቶ ገነት ገብቷል ሔዋንም በተፈጠረች በ፹ ቀኗ ልጅነትን አግኝታ ገነት ገብታለች ቤተ ክርስቲያናችንም ይህንን መሠረት በማድረግ ነው ወንዱን በ፵ ቀን ሴቷን በ፹ ቀን የምታጠምቀው በተጨማሪው ወላዲ ሴት በሕርስ የምትነፃበትን መሠረት በማድረግ ነው ዘሌዋ· ፲፪ ፣ ፩ — ፰ ተመልከት መጽሐፈ ኩፋሌ ፬ ፣ ፱ ላይም ብትመለከት በሰፊው ለመረዳት ትችላለህ ።



www.ethiopianorthodox.org

## የሴቶች ዓምድ

# ቤተ ክርስቲያንና ቤተ ሰብ

አዘጋጅ መዓዛ አስማማው

ጋብቻ ለቤተ ክርስቲያን ወሳኝ ነው ። ቤተ ክርስቲያንም በጋብቻ ለሚገኘው ቤተሰብ አለኝታ ናት ሁለቱ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን እናውቃለን ስለዚህም አንድ ሊቅ ሲናገር “ጋብቻ የዓለም እናት ናት ቤተ ክርስቲያንና ከተሞችን ትሞላለች ብሏል ። ሆኖም ቤተሰብ ለቤተ ክርስቲያን ቤተ ክርስቲያንም ለቤተሰቦቿ ምቹ የምትሆነው የተቀራረበና የተጠናከረ ግንኙነት ሲኖራቸው ብቻ ነው ።

ካልሆነ ግን የቤተሰብ ጭቅጭቅ በሚያስከትለው ችግር የምታዝነው ቤተ ክርስቲያን ናት። ይህ እንዳይሆን የቤተሰብዋን ፍላጐት ለማሟላት ባጭር ታጥቃ ማስተማር አለባት ። እምነቱን የሕይወቱ መመሪያ አድርጎ ራሱን ችሎ በመንፈሳዊ ሀብት በልጽጎ ሌሎችንም የኑሮው መሠረታውያን ነገሮችን አሟልቶ ፈጣሪውን እያመሰገነ ኑሮውን በሥርዓት ከሚመራው የላቀ እርስ በእርሱ ተለያይቶ በቤተሰቡ መካከል አድልዎና ጥላቻ ነግሠው ኑረው ሁሉ ለጭንቀትና ለትካዜ የተዳረገ ቤተ ሰብ እየተበራከተ መሄድ ቤተ ክርስቲያንን በጣሙን ያሳስባታል ።

ካለ እቅድ በላይ በላዩ የሚወለዱ ሕፃናት የእግዚአብሔር ስጦታዎች መሆናቸው መዝ ፩፻፳ ቁ ፫ ይዘነጋና እንደ ሸክም (እዳ) የሚታዩ ለችግር ለበሽታና ለጭቅጭቅ የተገኙ አድርጐ በመገመት በአስተሳሰብ ደክመው በእምነት ላልተው በመንፈሳቸው ወድቀው ማየት ቤተ ክርስቲያንን ጥሩ የሆኑ ተረካቢ ዜጎቿን ቁጥር ስለሚቀንስባት አሁንም የወንጌል መምህራንና የሚመለከታቸው ሁሉ ጠንክረው ማስተማር ይጠበቅባቸዋል ፤ በአንዳንድ ቤተሰብ መካከል የሚታየው ንዝንዝ በጋብቻ የሚገኘውን በረከት የሚያስነጥቅ እንጂ የተደላደለ ሕይወትና ጤናማ ኑሮ የሚያስገኝ አይመስልም ። ምክንያቱም ሰላምን ለማግኘት የባልና ሚስቱ ሐሳብ ተመሳስሎ አንድ ውሳኔ ላይ አለመድረስ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን አለማንበብ ፤ በዕረፍት ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሂዶ የሥርዐተ ቅዳሴው የጸሎቱ ተካፋይ ብቻ ሣይሆን በመምህራን የሚነገረውን የክርስቶስን ቅዱስ ቃል አለማዳመጥ የተነገረውን ቃል ተግባራዊ አለማድረግ የቤተሰብን ኑሮ መራራ ያደርገዋል ። እናት ዘወትር ለምታደርጋቸው ሥራዎች መወሰኛው የመርሐ ግብር (የሥራ ድርሻ) መኖር ዐቢይ ነገር ነው በዚህ የምትመራ ከሆነች ጭምት ሰዓት አክባሪ የቤተሰብ ባሕርይ በቀላሉ የማያነጫንጪት የማትሰለች ለመሆን ይረዳታል ። የቤቱን ኃላፊነት በቁጥጥር ሥር አድርጋ ለመጠበቅ ሙሉ እምነት ያድርባታል ።

ነገር ግን ፕሮግራም ለምኔ የምትልና ግደየለሽ ከሆነች ሕይወቷ በቀላሉ በክፋትና በጭንቀት ይዋጣል ። ቤቱም የፍቅር የሰላም ኑሮ የሚታይበት በረከተ እግዚአብሔር ያልተለየው መሆኑ ቀርቶ የርኩስ መንፈስ ማደሪያ ይሆናል። በዚያ ቤት ውስጥ ደስታ ፈጽሞ ይጠፋል ።

በቤት ውስጥ አባትና እናት የቤተሰቡን የኑሮ አቋም ቀያሾች (መሐንዲሶች) በመሆናቸው ያወጡትን (የቀየሱትን) መንገድ ራሳቸው ጠብቀው፤ ለቤተሰቡ ምሳሌ በመሆን ኑሮአቸውን በሥርዓቱ ይመራሉ ። አባት ቤተሰቡ ደፋሮች ታታሪዎች እንዲሆኑ ራሱን በቅድሚያ ጥሩ ምሳሌ አድርጎ ማቅረብ ያሻዋል ። በተለይም በረዳቱ በኩል የሞራል ድጋፍ በመስጠትና በመርዳት በመከታተል የሚያደርገው የሐሳብና የተግባር ተሳትፎ ረዳቱ ለምታወጣው መርሐ ግብርና ለምታከናውነው ሥራ መሠረት ያለው ስለማይሆን ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል ።

እናትም ብትሆን ከእግዚአብሔርም ሆነ ከረዳቷ ጋር የሚኖራት የቅርብ ግንኙነት ጥቅም ያለው ሊሆን የሚችለው ከቤተሰቦቿ ጋር በሚኖራት ፍቅር ሰላምና ተግባቢነትም ጭምር ነው በመሆኑም የቤት አያያዝ አዋቂ ጥቂቱን የምታበረክት ከቤተሰቦቿ ጋር ጤናማ ኑሮ የምታሳይ ከሆነች ከፈጣሪዋም ጋር የቅርብ ግኙነት ልታደርግ ትችላለች ።

ይሁንና ባልና ሚስቱ አንድ አካል የሆኑ ቤቱን የሚያዙና የሚያስተዳድሩ ናቸው ብንልም ርእስ (መሪ) ሊሆን የሚችለው ግን የሰላም ባለቤት የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው እግዚአብሔርን የኑሮአቸው ሁሉ መሪ አድ



ርገው ኑፋቄ (ጥርጥር) ባሌለበት እምነት የተቀበሉ ቤተሰቦቹ የተባረኩ ናቸው ። ከዚህም ሌላ ዘወትር ለሚከናወነው ተግባር አዲስ የአስተዳደርና የአሠራር የቤት አያያዝን የተከተለ መርሐ ግብር ባለመኖሩ የተነሣ እናት ከአባት አባት ከልጅ ልጅ ከእናት ተግባብተውና ሐሳብ ለሐሳብ ተለዋውጠው የጋራ ኑሮአቸውን ለማሸነፍ ይሳናቸዋል ።

አንድ ጊዜ በአንድ በማውቀው ሰላማዊ ቤተሰብ ውስጥ ያልታሰበ አለመግባባት እየተፈጠረ የነበረው ሰላም እየቀዘቀዘ በሚሄዱ ቤቱ እንዳልነበረ ሆኖ በማየቴ የቤተሰቡን ኃላፊ ወ/ሮ የሚከተለውን ጥያቄ አቀረብኩላቸው ። የበፊት ትዳራችሁ የተቃናና የተዋጣለት ነበር አሁን ግን እርስዎም ሆኑ ባለቤትዎ ግድየለሾች ሁናችሁ ነው የምትታዩት ልጆቻችሁም በመለያየት ፍቅራቸው እየቀነሰ ሄዷል ለምን ይሆን አልኳቸው ።

ወ/ሮዋም ሲመልሱ ኑሮአችንን አሸንፈን ለመኖር የምናደርገውን ጥረት ከእኛ አልፎ የውጪ ሰው ያውቀዋል ቢሆንም በዚያው ልክ ጭቅጭቁ የዚያኑ ያህል ነው። እሱም ከጊዜ በኋላ የመጣ እንጂ ቀደሞ አልነበረም ሌላው ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን ሁሉ ቤተ ክርስቲያን እንሄዳለን በተለይም እኔ በሰንበት ቀንም ሆነ በበዓላት ቀን ቤተ ክርስቲያን ሄጄ ስመለስ ከቤቴ የሚቆየኝ ነገር ነው ልጆቼ ያልኳቸውን አይሰሙም ቢሰሙም ጥቂቱን ነው በዚህ ምክንያት ሁልጊዜ ፍጅት ጨኸት ነው አሉ እየተማረሩ ።

በኋላም ለሚሠሩት ሥራዎች መርሐ ግብር አውጥተው ለልጆች አድለው እንደሆነ ብጠይቃቸው “ይሄማ እንዴት ይሆናል ዛሬ ተሠርቶ ተበልቶ ለሚያልቅ ነገር መሥሪያ ቤት አይደለ ወይም ት/ቤት አሉና መለሱልኝ “ለሁሉም ጊዜ አለው” የሚለው የጠቢቡ ሰሎሞን ትምህርት በአንዳንድ ምእመናን አእምሮ ቦታ ያገኘ ስለማይመስል በዚህም በኩል የቅርብ ጠባቂዎቻቸው የሆኑት የንስሐ አባቶቻቸውና በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ያሉት የወንጌል መምህራንም እንደየ አመቺነቱ ትምህርቱን የማስተላለፍና የማዳረስ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል ።

በአብዛኛው የቤተሰብ ኃላፊዎች እናቶች በመሆናቸው ልጆች የእናቶቻቸውን አብነት ይከተላሉ በቤት ያለውን የሥራ ድርሻ ለቤተሰቡ የሚያድሉም እነሱ በመሆናቸው ልጆች የእናቶቻቸውን ትእዛዝ ተቀብለው የተሰጣቸውን የሥራ ድርሻ በሚገባ ያከናውናሉ። መሪ አድርጎ መቀበል ብቻም ሣይሆን የራሳቸውን ትእዛዞች በደንብ አክብረው ሲገኙ በመካከላቸው ዘለዓለም ደስታ አይለያቸውም ከዚህም የተነሣ ቤተ ክርስቲያን የቤተሰቧ ፍላጐት ተሟልቶ በጥሩ ዓላማ ተከናውኖ ስትመለከት ደስታዋ የበለጠ ይሆናል ።

# ጾማችሁ እንደ ግብዞች አይሁን

ካለፈው የቀጠለ

ፈሪሳውያን ማለት በጣም መመጻደቅን የሚያበዙ ፤ ያለ እነርሱ ሃይማኖት ያለው ሁሉ ዋጋ እንደ ሌለው አድርገው የሚቆጥሩ፣ ከአምስቱ በሐውርተ ኦሪትና በቃል ከተላለፈላቸው ወግና ሥርዓት (ቶራ) ኦሪት በስተቀር ሌሎችን መጻሕፍት የማይቀበሉ ፤ አሕዛብን የሚጸየፉ ፤ ሁሉንም ኃጢአተኛ አድርገው የሚቆጥሩ ፤ የልማድ እሥረኞች ፤ ለሐዲስ ሥርዓት ነገረኞች ፤ ከነርሱም ወገኖች እንደ እነርሱ አጥብቀው የሙሴን ሕግ የማይጠብቁትን አይሁድን እንኳን ሳይቀር የሚንቁ ናቸው ። (ማር· ፯·፩— ፱ ፤ ሉቃ ፭ ፤ ፳፱—፴ ፤ ገላ ፩ ፤ ፲፬) መድኃኒታችንም በሚያስተምርበት ጊዜ ይቃወሙት ከነበሩት ወገኖች ፈሪሳውያን የመጀመሪያዎች ነበሩ ። እንነሳሳቸውም ከዮሐንስ ሕዝቃኖስ ጥቂት ቀደም ሲል በ፩፻፵ ዓመተ ዓለም ነበር ። እራሳቸውን ስለሚያመጻድቁም ሉቃ· ፲፰ ፤ ፲፩—፲፪ የተጠቀሰውን መመልከቱ በቂ ነው በየሳምንቱም ሰኞንና ሐሙስን ይጾማሉ ። ይህም ጾም ሐሙስ ሙሴ ወደ ደብረ ሲና ተራራ የወጣበት ሲሆን ፤ ሰኞ ደግሞ ከሲና ተራራ የወረደበት ዕለት ነው ። ይህንም ለሙሴ መታሰቢያ አድርገው ሁለቱን ቀናት በየሳምንቱ ይጾማሉ ። ስለዚህም ነው ሐዋርያት በ፩፻ ዓመተ ምህርት (በጻፉት) ዲድስቅልያ እየተባለ በሚጠራው መጽሐፍ “ጾማችሁ እንደ ግብዞች አይሁን ፤ እነርሱ ሰኞንና ሐሙስን ይጾማሉና ። እናንተ ግን ስትጾሙ ረቡዕንና ዓርብን ጹሙ” በማለት የጻፉልን ፤ እንድንጾምም ያዘዙን። በተለይ እኛ ደግሞ ረቡዕንና ዓርብን የምንጾምበት ምክንያት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን የሕማሙንና የሞቱን ዕለት እያስታወስን ነው ። ረቡዕን የምንጾመው አይሁድ በሊቀ ካህናቱ በቀያፋ ቤት ተሰብስበው በጌታችን ላይ ሲማከሩ ውለው በመጨረሻም



www.ethiopianorthodox.org

ሞት የሚገባው ነው በማለት የወ
ሰኑበት ስለሆነ ፤ (ዮሐ· ፲፩ ፣ ፵፯
፶፫) ዓርብን ደግሞ የምንጾመው
ረቡዕ ይሙት በቃ ብለው አይ
ሁድ የወሰኑትን ፍርድ በማጽናት
በዕለተ ዓርብ በአደባባይ በዕንጨት
ላይ ሰቅለው ስለ ገደሉት ለዚሁ
መታሰቢያ እድርገን እንጾመዋ
ለን ። ጾሙም የሚታወቀው ጾመ
ድኅነት በመባል ነው ።

መጥምቁ ዮሐንስ መድኃኒታ
ችን ሙሽራ ብሎ ይጠራዋል ።
(ዮሐ· ፫ ፣ ፳፱) ሙሽራ በሀገራችን
እጅግ በጣም ክቡር ነው ። በብ
ሉይ ኪዳንም ሙሽራ ወደ ዘመቻ
አይውጣ ይላል ። በመንፈሳዊም
ሆነ በሥጋዊ ነገር ሁሉ ለሙሽራ
ቅድሚያ ይሰጠዋል ። ለምሳሌ
በሀገራችን አንድ ወጣት በሚያገ
ባበት ጊዜ እርሱና ሚዜዎቹ ጾም
የተባለውን ሁሉ አይጾሙም ፤
እንዲጾሙም አይገደዱም ። ምክን
ያቱም ሚዜዎች የሙሽራው የደ
ስታ ተካፋዮች ስለሆኑና ሙሽራ
ውም የሙሽርነቱን ወራት እስኪ
ፈጽም ድረስ አብረው መደሰት
ስለ አለባቸው የሀገር ባህል ስለ
ሆነ ነው ። ይህንም ሥርዓት በማ
ቴዎስ ወንጌል ፱ ፣ ፲፬—፲፭ ብን
መለከት እናገኘዋለን ። (ማር· ፪ ፣
፲፰ ፣ ሉቃ ፭ ፣ ፴፫) ሙሽራውንና
ሙሽራይቱን የሚመለከታቸው
ምክንያት ቢኖር በሀገር ላይ አንድ
ችግር ሲፈጠር ብቻ ነው ይኸ
ውም ቸነፈር ፣ ረሀብ ፣ የጸጥታ
መደፍረስ ፣ ይህንና ይህን የመሰለ
በሀገር ላይ ሲደርስ በቤተ ክርስቲ
ያን የአስቸኳይ ጊዜ መንፈሳዊ
ዓዋጅ አለ ። ይህም ዓዋጅ በጾምና
በጸሎት ፤ በለቅሶ ፣ ምህላ በመያዝ፣
ወደ እግዚአብሔር መጮህ ነው ።
ይህም የምህላ ዓዋጅ እንኳንስ
የሰውን ዘር ይቅርና እንስሳትንም
የሚጨምር ሆኖ እናገኘዋለን ።
ያን ጊዜም ሁለቱ ሙሽሮች አብ
ረው ይጾማሉ አብረው ያዝናሉ ፤
አብረው ያለቅሳሉ ። (ኢዮ· ፪ ፤
፲፭—፲፯ ፣ ዮና· ፫ ፣ ፭—፰)

የዮሐንስ ደቀመዛሙርት
"እኛና ፈሪሳውያን ብዙ ጊዜ የም
ንጠመው ፣ ደቀ መዛሙርትህ ግን
የማይጠሙት ለምንድር ነው"?
በማለት በጠየቁት ጊዜ መድኃኒ
ታችን የሰጣቸው መልስ ሚዜዎች
ሙሽራው ከነርሱ ጋር ሳለ ሊያ
ዝኑ አይችሉም ፤ ነገር ግን ሙሽ
ራው ከነርሱ የሚወሰድበት ሰዓት
ይመጣል ። ያን ጊዜም ይጠማሉ ።
"በማለት የብሉይ ኪዳን ጾም ለሐ
ዲስ ኪዳን ጾም እንደ አዲስ እራፊ
ከአሮጌ ልብስ ጋር በማነጻጸር በሰ
ጠው መልስ ለመረዳት እንችላ
ለን። በተጨማሪም ከሞቱና ከትን
ሣኤው በኋላም በየዓመቱ ሕማ
ማተ መስቀሉን እንድናስታውስ ፤
የአርባውንም ቀን ጾም እንድን
ጾም እርሱ እራሱ ጌታችን በዚህ
ምዕራፍና ቁጥር በቃል ያስተማ
ረን ፣ በሥራም የገለጠልን መሆ
ኑን እንረዳለን ። ኢትዮጵያዊው
ቅዱስ ያሬድም ከዚህ ምዕራፍና
ከኢሳይያስም ትንቢት ፍሬ ሀሳብ
በመነሣት በራሱ ልሳን (ቋንቋ)
ትንሣኤ በዋለ በሰባተኛው ቀን
ስለሚዘመረው ስለ ቅዱሳት እን
ስት መታሰቢያ በጻፈው መዝ
ሙሩ "አዋልድ ምእመናት አጽም
ዓኒ ነገርየ ወለለዓመት ግበራ ተዝ
ካርየ" በማለት ያስተምራል ትርጓ
ሜውም ኢትዮጵያውያኑ ልጆቼ
ሆይ ምክሬን አዳምጡ ። በየዓመ
ቱም የሞት ኩበትንና የትንሣኡበ
ትን ዕለት እያስታወሳችሁ መታሰ
ቢያዬን አድርጉ ማለት ነው ።
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋ
ሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጾም ወራ
ቶች ተለይተው በቁጥር የተወሰኑ
ትና ሰባቱ አጽዋማት እየተባሉ
የሚጠሩት የሚከተሉት ናቸው ፤

፩ኛ) ጾመ ኢየሱስ ፤
፪ኛ) ጾመ ሐዋርያት ፤
፫ኛ) ጾመ ድኅነት ፤
፬ኛ) ጾመ ፍለሰታ ፤
፭ኛ) ጾመ ነቢያት ፤
፮ኛ) ጾመ ገሃድ ፤
፯ኛ) ጾመ ነነዌ ናቸው ። ከነዚህ
ሌላ የሚፈጸም ጾም ግን የፈቃድ
እንጂ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት
ተብሎ አይነገርም ። ከላይ ከተጠ
ቀሱት አጽዋማትም ትልቁ ጾም
ጾመ ኢየሱስ ነው ። በተለይም
በሀገራችን ከሌለች ሁሉ አብል
ጠን ሃምሳ አምበት ቀናት ስለምን
ጾመው "ዓቢይ ጾም" እየተባለ
ይጠራል ጾሙም የሚፈጸመው
በሦስት መዓልትና በሦስት
ሌሊት አክፍሎት ነው ። እርሱም
ከሐሙስ ማታ እስከ እሁድ መን
ፈቀ ሌሊት ያለው ሲሆን ይህንም
እራሱ ጌታችን ሐሙስ ማታ ለማ
ዕድ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ተቀ
ምጦ ሳለ "በአባቴ መንግሥት
አዲሱን የወይን ፍሬ ጭማቂ ዳግ
መኛ አልጠጣም ።" ሲል በንግ
ግር የመሠረተው ፣ በኋላም እርሱ
በመቃብር ፣ እነርሱ በኀዘን ሦስ
ቱን ቀናት አሳልፈው ከሙታን
ተለይቶ ከተነሣ በኋላ በገሊላ በተ
ገናኙ ጊዜ "አንዳች የሚበላ አላች
ሁን"? በማለት ጠይቆ የማር
ወለላ ከተጠበሰ ዓሣ ጋር አቅርበ
ውለት በፊታቸው በመብላት የፈ
ጸመው ነው ። (ማቴ· ፳፮ ፣ ፳፱ ፣
ሉቃ· ፳፬ ፣ ፵፩)

መሪ ጌታ ፀሐይ ብርሃኑ



# የአርባ ምንጭ ደብረ መድኃኒት መድኃኔ ዓለም የሰንበት ት/ቤት የተመሠረተበትን ፲ኛ ዓመት በዓሉን አከበረ

(ዘግይቶ የደረሰን ዜና)

በሰሜን ኦሞ ሀገረ ስብከት በአ
ርባ ምንጭ ከተማ የደብረ መድኃ
ኒት መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲ
ያን ሐምሌ ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ/ም
የሰነበት ት/ቤቱ የተመሠረተበ
ትን ፲ኛ ዓመት በዓሉን በደመቀ
ሁኔታ አክብሮ ውሏል ። ቀደም
ብሎ በወጣው መርሐ ግብር መሠ
ረት ከላይ በተጠቀሰው ቀን ልክ
በ፯፡፴ ላይ በተደረገላቸው የክብር
ጥሪ መሠረት ብፁዕ አቡነ ዘካር
ያስ የሰሜንና የደቡብ ኦሞ አህጉረ
ስበከት ሊቀ ጳጳስ እንዲሁም የሀ
ገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ መሪ
ጌታ ፈለቀ አየለ ፣ የሀገረ ስብከቱ
የመምሪያ ኃላፊዎች የአድባራት
አለቆችና መምህራን ካህናት በደ
ብሩ ያሉ የሰበካ ጉባኤ አባላት
ከየአውራጃውና ከአስተዳደር አካ
ባቢ ጥሪ የተደረገላቸው የሰንበት
ት/ቤት ተወካዮች እንዲሁም በአ
ካባቢው የሚገኙ ሕዝበ ክርስቲ
ያን በጠቅላላ በበዓሉ ላይ ተገኝተ
ዋል ።

በመርሐ ግብሩ መሠረት ብፁዕ
አቡነ ዘካርያስ ጥሪ ከተደረገላ
ቸው እንግዶች ጋር በመሆን በሰን
በት ት/ቤቱ ጽ/ቤት የሚገኙትን
የሥዕል ፣ የቅርጸ ቅርጽ ፣ የሥነ
ጽሑፍና ልዩ ልዩ የሆኑ የልማትና
የፈጠራ ሥራዎችን ከጉብኙ በኋላ
ብፁዕነታቸው በዓሉን በጸሎት
ከፍተዋል ።

ከዚያም በመቀጠል ባለፈው
ዓመት ያደረገውን የሥራ እንቅስ
ቃሴ ውጤት ሪፖርት በወጣት
ይልማ ካሣ የሰንበት ት/ቤቱ ሊቀ
መንበር ቀርቧል በቀረበው ሪፖ
ርት ሰንበት ት/ቤቱ የተቋቋመው
ከዚህ ቀደም በ፲፱፻፸፪ ዓ/ም ቢሆ
ንም ፈርሶ ከቆየ በኋላ በብፁዕ
አቡነ ዘካርያስ የሰንበት ት/ቤቱ
እንቅስቃሴ እንደገና እንዲቀጥል
ባደረጉት ብርቱ ጥረት በሐዲስ
መልክ በ፲፱፻፸፪ ዓ/ም ተቋቁሞ ።
በአሁኑ ጊዜ ሰንበት ት/ቤቱ
፩፻፶፪ የሚሆኑ የማኅበሩ አባላት
የሚሣተፉበት ሲሆን በዚህ
ዓመት የልማት ሥራዎችንና ብዙ
መንፈሳዊ ሥራዎችን እንዳከና
ወነ ተገልጿል ። ከዚህም ውስጥ
በተለይ በዐቢይ ጾም አባላቱ የየራ
ሱን የቁርስ ሂሣብ በማጠራቀም
ረጂና ጠያቂ የሌላቸውን ድኩማ
ንና ችግረኞችን ለመርዳት ባደረ
ገው ጥረት የትንሣኤን በዓል ተደ
ስተው እንዲውሉ የተቻለውን
ዝግጅት በማድረግና እንዲሁም
በየዓመቱ የደብረ ታቦርን በዓል
በከፍተኛ ደረጃ የቆሎ የዳቦና
የጠላ ዝክር በማቅረብ ለሌላው
በአርአያነትና በምሳሌነት የሚጠ
ቀስ ተግባር አከናውኗል ። ይህ
የሰንበት ት/ቤት በየጊዜው ትምህ
ርት አዘል የሆኑ መንፈሳዊ ድራማ
ዎችን በማዘጋጀት በአካባቢው
ባሉት አብያተ ክርስቲያናትና በየ
አውራጃዎች በመሄድ ምእመና
ኑን በመቀስቀስና የበለጠ ትምህ
ርት እንዲቀስሙ ከፍተኛ ጥረት
ማድረጉን በሪፖርቱ በዝርዝር
ተገልጿል ።

ከዚህ በማያያዝ በመምህሩ
በመሪጌታ እውነቱ ይሁን የተዘ
ጋጀ "ጠንቀቅ ከሚነጥቅ ፈቀቅ
ከማናፍቅ" በሚል የትምህርት
ጭውውት በ፪ ወጣቶች ከቀረበ
በኋላ ለበዓሉ የተዘጋጀ ድራማ
ታይቷል ይኸውም የራሄል እንባ
በሚል ርዕስ ሲሆን ይህንን አስደ
ናቂና አሳዛኝ ድራማ እጅግ በጣም
በብዛት የሚቆጠር ሕዝብ በተመ
ስጦ እና በከፍተኛ አድናቆት
ሲመለከት ቆይቷል ። ከዚያም
ድራማው ታይቶ እንዳበቃ የሰን
በት ት/ቤቱን በበጐ ፈቃድ ላስተ
ማሩ መምህራንና ከየአውራጃው
ለዚህ በዓል ጥሪ ተደርጐላቸው
ለመጡ የሰንበት ት/ቤት ተወካ
ዮች እንዲሁም በልዩ ልዩ ሥራ
ለተሣተፉ ለማኅበሩ አባላት ሽል
ማትና የምሥክር ወረቀት ተሰጥ
ቷል የምስክር ወረቀቱን የሰጡት
ብፁዕ አቡነ ዘካርየስ የሰሜንና
የደቡብ ኦሞ ሀገረ ስብከት ሊቀ
ጳጳስ ናቸው ብፁዕነታቸው የምስ
ክር ወረቀቱን ከሰጡ በኋላ አባታ
ዊና መንፈሳዊ ምክራቸውን
ሲሰጡ "አሐዱ እግዚአብሔር
አሐቲ ሃይማኖት ወአሐቲ ጥም
ቀት" እግዚአብሔር አንድ ነው
ሃይማኖትም አንዲት ናት ጥምቀ
ትም እንዲት ናት "ኤፌ·ም·፬·
ቁ·፭ በማለት በነዚህ ጥቅሶች
ኃይለ ቃል ላይ በመመርኮዝ ብፁ
ዕነታቸው ሰፋ ያለ ትምህርት
ከሰጡ በኋላ ወደ ሊቃውንት ድር
ስት (ጸሎተ ሃይማኖት) ገባ በማ
ለት አሐቲ ቤተ ክርስቲያን ቤተ
ክርስቲያን አንዲት ናት በወርቅ
በዕንቁ በብር በጭቃ በጨፈቃ
ብትሠራም አንድ እግዚአብሔር
ስለሚመለክባት የአንድ የክርስ
ቶስ ሥጋና ደም ስለሚቀርብባት
ቤተ ክርስቲያን አንዲት ትባላለች
በእግዚአብሔር አምነው በአን
ዲት ቤተ ክርስቲያን ተማፅነው



www.ethiopianorthodox.org

የሰንበት ት/ቤት ወጣት አባላት የሚያከናውኑት መንፈሳዊ ሥራም በጣም አስደናቂ ነው እነርሱም ምንም እንኳ ሴት ወንድ ቀይ ጠይም ቀይ ዳማ ወጣት ታዳጊ ወጣት ሕፃን በሚል በፆታና በእድሜ ደረጃ ስያሜ የተለያዩ ቢሆኑም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ሥር ተሰባስበው የሚያሳዩት የሥራ ፍሬ እንደ ንቦች ማር የጣፈጠ ነው ።

ስለዚህ ሲራክ ጥበብ በተመላበት መጽሐፍ እንዲህ ብሏል ቀደኃ በጥበቡ ይከበራል በመኳንንትም መካከል ይቀመጣል ፤ መልክ መልካም ነው ብለህ ለሰው አታድላ መልክ ጥፉ ነው ብለህ ሰውን አትናቀው ንብ ከወፎች ሁሉ በመልክ ትከፋለች ማሯ ግን ከሁሉ ይጣፍጣል "መ.ሲራክ ም.፲፩ ቁ.፩ -፫ ንብ በተፈጥሮዋ አነስተኛ ስትሆን የምትሠራው ማር ግን ከሁሉ የጣፈጠ እንደሆነ መንፈሳውያንና መንፈሳዊያት የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች በአቅም በቁመት በእድሜ በኃይል የተለያየ ደረጃ ቢኖራቸውም በአንዲት ተዋህዶ ሃይማኖታችን ፀንተው የሚሰጡት መንፈሳዊ ተልዕኮ እጅግ ያማረና የተወደደ የተቀደሰም ነው በማለት ብፁዕነታቸው ትምህርቱን ካገባደዱ በኋላ ቿ፩ መጻሕፍትን የያዘ ፩ መጽሐፍ ቅዱስና የተለያዩ የመማሪያ መጻሕፍትን እንዲሁም ለሰንበት ት/ቤት ማደራጃ የሚሆን ገንዘብ ከሀገረ ስብከቱ ሰጥተው ጸሎተ ቡራኬ በማድረግ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል ።

# ጤናችን

(ካለፈው የቀጠለ)

ከመ/ሕይወት ይትባረክ ዓለሙ

ለምሳሌ ውሀን በንጽሕናና በትክክለኛ መንገድ በመጠቀም የተቅማጥ በሽታን ለመከላከል ይቻላል ።

በብዙ ቦታዎች ለልጆች ሕመምና ሞት ዋናው ምክንያት የተቅማጥ በሽታ ነው ። የተቅማጥም ሕመም መንስኤው የተበከለ ውሃ ነው ።

ስለዚህም ተቅማጥን ለመከላከል የሚያስችለው ዓይነተኛ ዘዴ ለመጠጥና ለምግብ ማዘጋጃ የሚሆነው ውሃ የተፈላና በጥንቃቄ የተያዘ መሆን አለበት ። የልጆች መመገቢያ ዕቃዎችም (ቁሳቁሶች) በሚገባ መቀቀል ይኖርባቸዋል ። ምግብን ከማዘጋጀትና ከማቅረብ በፊት ከተመገቡም በኋላ እጆችን በውሃና በሳሙና ሙልጭ አድርጐ መታጠብ በጣም ጠቃሚ የሆነ የበሽታ የመከላከያ ዘዴ ነው።

በልጆች የሚደርሰው ተቅማጥ በቀላሉ ለሞት የሚያበቃበት ዋና ምክንያት ከሰውነታቸው ብዙ ፈሳሽ ሲወጣ በሚደርስባቸው የሰውነት መድረቅና (ዴሃይድሬሽን) ልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች ማጣት ነው።

ስለተቅማጥ እነሣሥና ሊደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ ተገልጿል መጠንቀቁ እጅግ ጠቃሚ ነው ሲራክ "ዘእንበለ ትሕምም ተፈወስ" ሳትታመም ዳን ያለውም ከዚህ የተለየ አይደለም ። ከጥንቃቄው ጋር ደግሞ እግዚአብሔርን ማመን ያስፈልጋል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሥጋን ለብሶ በዚህ ዓለም እየተመላለሰ ያስተምርበት በነበረው ዘመን ፴፰ ዓመት በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ተይዞ የኖረውን መጻጉዕን ከእናቱ ማኅፀን እውር ሆኖ የተወለደውን በሽተኛ በሆድ ዝማ (በትቅማጥ) ተይዛ ስትጨነቅ የነበረችውን የጴጥሮስ አማት ፈውሷል ፤

ስለዚህ ከታመሙም በኋላ ሆነ ሳይታመሙ ማዳን የሚችለውን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከዶክተሮችና ከሐኪሞች በላይ የጤናና የድኅነት ባለቤት አድርገን ዘወትር መመልከቱ ይጠቅማል ቢታከሙም መድኃኒትም ቢወስዱም ያለ እግዚአብሔር ቸርነት ለመዳን አይቻልምና ።

የዜናው አቅራቢዎች
፩. ወ/ሪት ሃይማኖት ተካ የሀገረ ስብከቱ የሰ/ት/ቤት ተጠሪ ።
፪. መ. እውነቱ ይሁን የሰንበት ት/ቤቱ መምህር



# ወጣቶች በወላጆች እግር ሲተኩ

የመናገሻ ቅ/ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተ ከ፩፻፷ ዓመት በላይ ሆኖታል ፤ ይህ ቤተ ክርስቲያን በተተከለበት ዘመን ብዙ ሊቃውንት ነበሩበት ከዚህም የተነሳ መንፈሳዊ አገልግሎቱ እጅግ በጣም የተጠናከረ ነበር ።


ይህ ቤተ ክርስቲያን በአሁኑ ሰዓት ሊቃውንቱ በሞት እየተለዩት በመሆናቸው የካህናቱ ቁጥርና የአገልግሎቱ ሁኔታ በጣም የተዳከመ ሆኖአል ።

ይህ ሁኔታ ያሳዘናቸው የደብሩ አካባቢ ጠቅላላ ተወላጆችና ነዋሪዎች ለአገልግሎቱ መጠናከር በጋራ ይተባበራሉ ሆኖም የታሰበውን ያህል ተሟልቶአል ባይባልም አሁንም የቦታው ነዋሪዎች በስብሰባ ጉባኤ አማካይነት በወርና በዓመት የሚከፈለውን አስተዋጽኦ በመክፈል የሚቻላቸውን ያህል እያሟሉ ይገኛሉ ።

ይህም አፈጻጸም ለአገልግሎቱ መቃናት በቂ ሆኖ ባለመገኘቱ በአዲስ አበባና በየክፍለ ሀገሩ የሚገኙ የቦታው ተወላጆች በዚህ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ በጥቅምት እና በሚያዝያ ፴ በዓመታዊ በዓሉ ላይ በመገኘት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ።

በተለይ በአዲስ አበባ የሚገኙ የአባ ወ/ሐና — ተወላጆች ለቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ሕልውና በሰበካ ጉባኤ አባልነት በየወሩ አስተዋጽኦ ከማ[illegible]ጋቸውም በላይ በአሳብ ፤ በጉ[illegible]ና በሚጠየቁት ሁሉ ይረዳሉ[illegible]

መልካም ዘር ከነአገዳው[illegible] እንዲሉ ይህን በጎ ዓላማ የተመለከቱና የወላጆቻቸውን መሠረተ ዓላማ የመረመሩ ልጆቻቸው ደግሞ ወላጆቻቸው ሲያደርጉት የነበረውን መልካም ሥራ በመከተል "<u>በአባ ወልደሐና እና በአባ ወ/ማርያም</u>" ስም በየወሩ እየተሰበሰቡ ሥጋዊ ዝምድናቸውን ከማጠናከር ጋር በመንፈሳዊ ሕይወታቸውም በኩል የቅዱስ ማርቆስን ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት በጉልበትና በሚችሉት አቅም ሁሉ ለመርዳት ወስነዋል።


የቅዱስ ማርቆስ የሰንበት ተማሮች በከፊል

እኒሁ <u>የአባ ወ/ሐና እና የአባ ወ/ማርያም</u> ተወላጆች ክፍል ሁለት የሆኑት አባላት የአንደኛ ዓመት መንፈሳዊ በዓላቸውን መስከረም ፳ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም ባከበሩበት ወቅት ከቦታው ተገኝተን የማህበሩን ዓላማና ሒደት መዝግበናል ።

በዕለቱ የማኅበሩ ታዳጊ አባላት የማኅበሩ ቀዳሚና አንጋፋ ወላጆች አባቶችና እናቶች ... አባላት በዕድሜ ከፍ ያሉ ወላጆች እህቶችና ወንድሞች ከስብሰባው ቦታ ተገኝተው በዓሉን በጋራ አክብረዋል ።

በዕለቱ አንድ ካህን እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ጸሎት ካደረጉ በኋላ በመርሐ ገብሩ መሠረት በቅደም ተከተል የበዓሉ ሥነ ሥርዓት ተከናውኖአል ።

እንደ ቅደም ተከተሉም የማህበሩ ሰብሳቢ ሀብታሙ ለይኩን አጭር ሪፖርት አሰምተዋል ።

<u>ከሪፖርቱ የተወሰደ ፍሬ ቃል</u>

፩/ጭንቀት ቀን ሳይመጣ ፤ ደስ አያሰኙኝም የምትላቸው ዓመታት ሳይደርሱ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ መ/መ.ክ ፲፪ ቁ፩ — ፪ እንደተባለው አባቶቻችንና እናቶቻችን ከዚህም ጋር የእኛ የበላይ የሆኑ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች በመሆናቸው ለቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን



www.ethiopianorthodox.org

ሕልውና ያደርጉት የነበረውና አሁንም የሚያደርጉት አስተዋጽኦ ከልብ ይሰማናል ፡ ስለሆነም እኛም ልጆቻቸው እግዚአብሔር ለዚህ ቁም ነገር ካበቃን ከዚህ የወጣትነት ዕድሜአችን ጀምሮ የሃይማኖታችን አባት ለሆነው ለቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት ማሟያ የሚውል በየወሩ ዜሮ ፲ ሣ· በማዋጣት ከ፶ አባላት በዓመት ብር ፰ (ስድሳ ብር) ለቤተ ክርስቲያኑ ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት በሕጋዊ ደረሰኝ ማስረከብ ከማህበራችን ዓላማ አንዱ ነው ።

፪/ ይህም ክፍያ በየዓመቱ ከፍ እያለ የሚሔድ ሲሆን ለዓላማው ተግባራዊነት የአባቶች ጸሎት እንዳይለን እንለምናለን ፡ ይህን ዓላማ ብርቱና ጠንካራ ለማድረግ ያስችለን ዘንድ እንዲሁም ስለሃይማኖታችን ፡ ስለሀገራችን ፡ ስለወገኖቻችንና በጠቅላላ ስለመንፈሳዊ አቅዋማችን ትምህርትና መመሪያ የሚሰጠን አንድ መንፈሳዊ ካህን ከቤተ ክህነት የሚመለከተው ክፍል እንዲመደብልን ማህበሩ ይጠይቃል ።

፫/ በቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በዓመት ፩ ጊዜ በመገኘት የልማት ሥራ የጽዳት ሁኔታ ተምሮ የማስተማር ሒደት እንዶት እንደሆነ ከወላጆች ጐን ተሰልፎ የሚገባውን ያካሒዳል ።

፬/ በቅርብ ጊዜ የተቋቋመው የቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን እድሳትና ልማት ኮሚቴ በሚልከን አቅጣጫ ሁሉ ተሰልፈን የልማቱን ሒደት ለማጠናከር ደንባችን ይፈቅዳል ።

፭/ ዓላማችን በሰንበት ት/ቤት ተኮትኩተን ከዚህ ደረጃ የደረሰን በመሆናችን በቃለ ዓዋዲው ደንብ ም.፬ አንቀጽ ፲፭ በተደነገገው መሠረት ከአሁኑ ጀምሮ በእምነታችን መሠረት ሃይማኖትን አጽንተን ለወደፊትም ለሰበካ ጉባኤ አባልነት ያለማንም ጉትጐታ የምንሰለፍ መሆናችንን የማህበራችን መመሪያ ያረጋግጣል ።

፮/ የማህበራችን አባላት በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ፀንተው ተጠናክረው በግብረገብነትም ታንጸው እንዲኖሩ በአባቶች እግር እንዲተኩም በየዕለቱ የወላጆች ምክር በየወሩ የካህኑ ትምህርት አስፈላጊያችን መሆኑ ታውቆ የወላጆች አሳብና ድጋፍ እንዳይለየን በማህበራችን ስም እንጠይቃለን ።

በተረፈ እግዚአብሔር ለሀገራችን ለኢትዮጵያ ሰላምን ለሕዝቡ አንድነትና ጤንነትን እንዲሰጥልን እንመኛለን ሲል ሪፖርቱን ደምድሞአል ።

በእኛም በኩል ይህ ዓይነቱ አሠራር እንደምሳሌ ሊጠቀስና ሌሎችም የቤተ ዘመድ ስብሰባዎች በወጣትነት ደረጃ የሚገኙ ልጆቻቸው በዚህ ዓይነት እየተሰበሰቡና ሃይማኖታዊና ብሔራዊ ባሕላቸውን እንዲያጠኑ ቢደረግ ይጠቅማልና ይታሰብበት ።

የአባ ወ/ሐናና የአባ ወ/ማርያም ተወላጆችም የጀመራችሁት ዓላማ ራሳችሁንና ፣ ወላጆቻችሁን ቤተ ክርስቲያናችሁን ፣ አገራችሁን ወገኖቻችሁን እንድትወዱ እንድታከብሩና እንድትከተሉ የሚያስችላችሁ በመሆኑ በዓላማችሁ ግፉበት ፣ በተለይም የካህኑ መኖር ጠቃሚ ስለሆነ በሕጋችሁ ተጠቀሙበት ።

በ፩ኛ ጢሞ.ም.፬.ቁ.፲፪ ላይ "በቃልና በኑሮ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑት ሁሉ ምሳሌ ሁን እንጂ ታናሽነትህን ማንም አይናቀው" ተብሎ እንደተጻፈው መንፈሳዊውን ተግባር ከሥጋዊ ጋር አስተባብራችሁ ለመያዝ በርቱ የቤተሰቦቹን መልካም አርዓያ የማይከተል ግን ሃይማኖቱን እንደተወ ይገመታልና ።

የዜናው አቅራቢ

ሊ.ካ. በለጠ አበበ

# ዮም ተወልደ ቤዛ ኩሉ ዓለም

ዓለምንና በውስጡ የሚገኙትን ፍጥረታት ሁሉ መግቦና ጠብቆ የሚኖረው አምላካችን እግዚአብሔር የቅድስት ድንግል ማርያምን ሥጋ ተዋሕዶ ማለት በድንግልና ተፀንሶ ታህሣሥ ፳፱ ቀን እኛን ሰዎችን ከዲያብሎስ ቁራኝነት ለማላቀቅና ቤዛ ለመሆን ተወለደ።

እግዚአብሔር አምላካችን አባታችን አዳምን እናታችን ሔዋንን በርሱ አምሳል እርሱን አስመስሎ ፈጥሮ የብርሃን ልብስ አጎናጽፎ በተድላ ገነት ከማስቀመጡም ጋር የዚህ ዓለም መሪ አስተዳዳሪ እንድትሆኑ ፈቅጃላችኋለሁ ነገር ግን በገነት መካከል ዕፀ በለስ የምትባል ስለአለች ከርሷ ፍሬ እንዳትበሉ የበላችሁ እንደሆነ የሞት ሞትን ትሞታላችሁ ብሎ አስጠነቀቃቸው ። በዚህም ሁኔታ አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር አምላካቸው ያዘዛቸውን ትዕዛዝ ጠብቀው ሰባት ዓመት በገነት ኖሩ። ከዚህ በኋላ የሰው ልጅ ጠላት ዲያብሎስ በኑራቸው ስለቀና እግዚአብሔር አምላክ ያዘዛቸውን ትእዛዝ አስፈርሶ የበለስን ፍሬ እንዲበሉ አደረጋቸው በዚህ ጊዜ ልብስ ብርሃናቸው ተገፎ ራቁታቸውን ሆኑ ከገነትም ወጥተው ተባረሩ ይህ ብቻ ሳይበቃቸው በነፍሳቸው ደግሞ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሙሉ በመንፀፈ ደይን ወድቀው በእግረ አጋንንት ተጠቅጥቀው እንዲኖሩ እግዚአብሔር ፈረደባቸው ። አዳምና ሔዋንም አዘኑ አለቀሱ እግዚአብሔርም የአዳምንና የሔዋንን ኃዘንና ልቅሶ ተመልክቶ ከሰማይ ወርጄ ከድንግል ማርያም ተወልጄ በመስቀል ተሰቅዬ ሙቼ ተነሥቼ በከቡር ሥጋዬ በቅዱስ ደሜ አድናችኋለሁ ብሎ ተስፋ ሰጣቸው ።

አዳምና ሔዋንም ተስፋውን አምነው በጾምና በጸሎት ተወስነው እያዘኑ እያለቀሱ ኑረው ከአለፉ በኋላ ልጆቻቸው የልጅ ልጆቻቸው አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን በጨለማ ከቆዩ በኋላ ይቅርባይ አምላካችን ቀጠሮውን አክብሮና ጠብቆ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ተፀንሶ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ፣ ከቆየ በኋላ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን በኢየሩሳሌም ከተማ በቤተልሔም አውራጃ ተወለደ ።

ክርስቶስ ከተወለደ ወዲህ ያለውም ዘመን ዓመተ ምሕረት ተባለ ። ዓ/ም ማለትም የምህረት የይቅርታ የሰላም ዘመን ማለት ነው ። ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው ዘመን ግን ዓመተ ዓለም ዓመተ ኩነኔ ዓመተ ፍዳ ይባል ነበር ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደም ጊዜ አህያና ላም በትንፋሻቸው አሞቁት እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም በጨርቅ ጠቅልላ በግርግም አስተኛችው ቅጠልም አለበሰችው በዚያም ምድር መንጋቸውን በሌሊት ሲጠብቁ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ መልአክ ወደ እነርሱ ቀርቦ እነሆ እኔ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ የምሥራች እነግራችኋለሁ ዛሬ በዳዊት ሀገር ቤተልሔም የዓለም ሁሉ መድኃኒት የሚሆን ክርስቶስ ተወልዶላችኋልና አትፍሩ ብሎ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል አበሠራቸው እረኞቹም ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ እያሉ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ፈጥነው ወደ ቤተልሔም ሔዱና ቅድስት ማርያምንና ዮሴፍን ሰሎሜን ሕፃኑን ኢየሱስንም በበረት ተኝቶ በጨርቅ ተጠቅልሎ አግኝተው አመሰገኑት ዜናውንም ላልሰማ አሰሙ ሰብአ ሰገልም በኮከብ እየተመሩ ሔደው ሕፃኑ ከተወለደበት ቤተ ልሔም ሲደርሱ በግንባራቸው በመስገድ ወርቅ ፣ ዕጣን ፣ ከርቤ አበርክተውለት ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል።

ስለዚህ በክርስቶስ እምነት ያለን ሁሉ እነሆ ዛሬ የዓለም ሁሉ መድኃኒት ተወለደልን ፣ ይቅርታ ተደረገልን ፍቅር ተመሠረተልን ስለሰው ፍቅር ብሎ ከሰማይ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወለደልን እያልን በየዓመቱ ታኅሣሥ ፳፱ ቀን እናከብረዋለን በዚህ ዕለትም የበዓሉን ሥነ ሥርዓት በልዩ ልዩ ባሕል በከፍተኛ ደስታ እንገልጻለን ። እንኳንስ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ዕለት እኛ እንኳን የተወለድንበትን ዕለት በየዓመቱ እናከበረዋለን ።

በተለይ በላስታ ሮሃ በዓለም በታወቀው በቅዱስ ላሊበላ ቤተ ክርስቲያን የጌታችን ልደት ለማክበር በኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር የሚገኙ ምእመናን አንድ ወርና ፲፭ ቀናት በእግራቸው ተጉዘው ታኅሣሥ ፳፱ ቀን ከቦታው በመድረስ በዓሉን በደመቀ ሁኔታ ያከብራሉ። ዓይኔ ዓለም አየ እግሬ ደርሶ የድንጋይ ወጋግራ የደንጋይ ምሰሶ እረ እንደምን እድርጐ አነፀው እንደምን አድርጎ ሠራው ፣ እረ እንደምን ያለ ጠቢብ ነው እረ እንደምን ያለ እጅ ነው ውስጡ አረንጓዴ ነው ባሕር እያሉ ደስታቸውን ይገልጻሉ ካህናቱና መዘምራኑ ደግሞ በማሚጋራው በሕንፃው ዙሪያ ሁነው መቋሚያና ጸናጽላቸውን ይዘው ካባና ጥንግ ድርባቸውን ለብሰው በግንባራቸው እየሰገዱ በእግራቸው እያሸበሸቡ በእጃቸው እያጨበጨቡ ዮም ተወልደ ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ ከሣቴ ብርሃን እያሉ ሲዘምሩ የተመለከተ ሁሉ አድናቆቱን በአንክሮ ይገልጣል ። በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በታነፁ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ታቦት ወጥቶ ሁደት ይደረጋል ። የክርስትና እምነት ያላቸው ነገሥታትም በአዳራሽ ተገኝተው እንኳን ለብርሃነ ልደቱ አደረስዎ የሚለውን ሕዝባቸውን ይቀበላሉ ስለበዓሉም ታላቅነት ነገሥታቱ ግብዣ አድርገው ያበላሉ ያጠጣሉ የሚሸልሙትንም ይሸልማሉ ፣ ምእመናኑም እርስ በእርሳቸው እንኳን ለብርሃነ ልደቱ አደረሳችሁ ይባባላሉ ። ጠቅላላ በክርስቶስ ልደት ሁሉ እየተደሰተ እርፎ ይውላል በየቤቱም ይገባበዛል ። ለሕፃናትም አዳዲስ ልብስና ጫማ የሚገዛላቸው ፣ ስጦታ የሚደረግላቸው በልደት ሰሞን ነው ጠላው ዳቦው እንጀራው በየቤቱ ይዘጋጃል ስለዚህ የሁሉም ደስታ እጽፍ



www.ethiopianorthodox.org

# የድሮ ቅርስ ሁልጊዜ አዲስ

ይህንን ለማለት ያስፈለገበት ምክንያት ተረት እያደረ እውነት ይሆናል የሚባለው ሣይሆን ታሪክ እያደረ እየሸተ ይሄዳል እንደሚለው ያለ ነው ። ከዚህ በላይ የተጠቀሰው አነጋገር ምሣሌውን ወደ ትርጓሜ ስንለውጠው በኢትዮጵያ ውስጥ አሉ ከሚባሉት አንጋፋ ታሪኮች አንደኛውና ጎልቶ የሚታየው በቅርፅ ታዋቂው የቅዱስ ላሊበላ ሕንፃ ነው ። ስለዚህ ሕንፃ መተረክ ወይም ማውሣት የሚቻለው በብዙ ሊቃውንትና የቴክኒዎሎጂ ምሁራን ተጠንቶ ቢቀርብ ነበር ። ነገር ግን "ማንይንገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ" እንዲሉ ፤ እኔም እንዳየሁት እመሠክራለሁ እንደሰማሁት እናገራለሁ ።

የነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ጥንተ ነገርና አመጣጥ እንዴት ነው ቢሉ እግዚአብሔር አምላክ በወዳጁ በቅዱስ ላሊበላ ላይ አድሮ የባሕርይ አምላክነቱን የገለጸበት የባሕርይ ቸርነቱንም ያሣየበት ነው ለማለት ይቻላል ። አንዳንድ ስለቅዱስ ላሊበላ ታሪክ እንናገራለን የሚሉ አባቶች ታሪኩንም ሆነ ዓመተ ምህረቱን (ክፍለ ዘመኑን ሳያስተካክሉ ይጽፋሉ ።

ይኸውም ጽሑፍ ወደ ቦታው ሲመጣ ከገድሉ ጋር ስናነፃፅረው የማይመሣሠልና ባዕድ ታሪክ ነው ። በዚህ አይነት ስለቅዱስ ላሊበላ መንግሥትና ሕንፃ መሠረት ገድሉ ብቻ ሣይሆን የውጭ ሀገር የታሪክ ምሁራን አስተካክለው አስቀምጠውታል ። እኔም ይህን ሁሉ ለመናገር ያስገደደኝ ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸው የታሪክ መዛባት ብቻ ሳይሆን ከላሊበላ አብያተ ክርስቲያናትም አንዱ የሆነው ቤተ መርቆርዮስ በ፲፱፻፷ ዓ.ም በመፍረሱ ነው ። በ፲፱፻፶፰ ዓ.ም ሚስተር አንጀሊኒና ሚስተር ቸካ የተባሉ የኢጣልያ ተወላጆች የዚህን ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ አሻሽለን እንሠራለን ብለው አፍርሰው ታቦቱም ወጥቶ ወደ ቤተ አማኑኤል ተደርቦ ለ፳፪ ዓመት ቆይቷል ። የኸውም ቤተ መቅደስ የልዩ ልዩ አራዊት ምሽግ በመሆኑ ካህናቱና ምእመናኑ ተሰብስበው በአባ ዘካርያስ ዋሴ አስተባባሪነት እንዲሠራ በመወሰኑ ሊሠራ ችሏል ። የሥራው ሒደት እንደሚከተለው ነው ።

1– ኮሚቴ በማቋቋም

ሊቀ መንበር ቄስ አበጀ ደሣለኝ
ምክትል ሊቀ መንበር አቶ ሰፊነው ተገኘ
ዋና ፀሐፊ አፈሊቃውንት ገብረ ማርያም ደሴ
ገንዘብ ያዥ አቶ ገብረ ማርያም መድፉ
ካርኒ ቆራጭ ወታደር አብርሃም ተገኘ
የእቃ ግምጃ ቤት ዲያቆን በላይ እናውጥ
ተቆጣጣሪ ዲያቆን ዘውዴ አላምረው
የኮሚቴ አባል ሀብቴ ባየ

የሰንበት ተማሪዎች የቅርብ ተጠሪዎች በመሆን ተመርጠው ሥራው ጥቅምት ፳ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ.ም ተጀምሮ ታኅሣሥ 6 ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ/ም ተፈጽሞ ታኅሣሥ ፲፫ ቀን ፲፱፻፹፪ ዓ/ም እሁድ የብርሃን ዕለት ታቦተ መርቆርዮስና ታቦተ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በሰላም ወደ ቤተ መቅደስ ለመግባት ችለዋል ። የአሰራሩም ሁኔታ አስቀድሞ ተመሣሣይ የሆነ ጥርብ ድንጋይ ተዘጋጅቶ በመገኘቱ የሕንፃ ሥራልምድ ባላቸው በአቶ አጎናፍር ማሞ መሪነት በአማረና በተዋበ ሁኔታ ተጠናቋል ። የዚህም ሕንፃ መታደስ በአካባቢው ያሉትን ካህናትና ምእመናን ብቻ ሣይሆን ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ እንደሚያስደስት እንተማመናለን ምክንያቱም የፈረሰው ታድሷል የጎደለው ተሞልቷልና ነው ።

ከዚህ ቀጥሎ በቅዱስ ላሊበላ የሚገኘው የቅዱስ መርቆሬዎስ ታቦት የሠራውን ተአምር ጥቂት እንናገራለን ። በአፄ ናዖድ ዘመነ መንግሥት ይህንኑ ቤተ መቅደስ ቄሰገበዙ ጠንቅቆ ባለመዝጋቱ ሌባ ገብቶ ታቦቱንና ንዋየ ቅድሳቱን ዘርፎ ሢሔድ የሦሥት ሰዓት መንገድ እንደሔደ ሰኞ ገበያ ከተባለው ቦታ ሲደርስ ፅላቱ እንደ እሳት ቢፈጀው ከልብሱ በላይ አስቀምጦ ትቶት ሔዷል በአካባቢው ያሉ ሰዎች ግን አሻግረው ሲመለከቱ እሳት እየነደደ ክምር የተቃጠለ መስሎአቸው ተሰብስበው ቢሔዱ ፅላቱ በብርሃን ተከቦ ሢያበራ አግኝተውታል ከዚያም ካህናት ተጠርተው ፅላቱ በክብር ተነስቶ ሲነበብ "ዝ ታቦት ታቦተ መርቆርዮስ ዘተከሎ ቅዱስ ላሊበላ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ" የሚል ሆኖ በመገኘቱ ወደ ቤተ መቅደሱ ተመልሷል ። ይኸውም ቦታ እስከዛሬ ድረስ መርቆሬዎስ በር እየተባለ ይጠራል ። ቅዱስ ላሊበላ በዘመኑ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቢገኙም በግዛቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ዝቋላ የሚባል ቦታ ሠጣቸው እንጂ ቤተ መቅደስ በስማቸው አልሠራላቸውም ነበር ። ምክንያቱም እሳቸው በሕይወተ ሥጋ ስለነበሩ ነው ። በኋላ ግን በ፲፱፻፳፮ ዓ.ም መሪጌታ ተሠራ አየለ የሚባሉ ሊቅ ባነሣሡት አሳብ ማኅበሩ ተስማምቶ ታቦተ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ከታቦተ መርቆሬዎስ ጋር ደርበውታል ። ስለዚህ የአባታችን የገብረ መንፈስ ቅዱስ ስዕለት እየበዛ ምዕመናንም እየጨመሩ ከመሔዳቸው የተነሣ ቤተ ክርስቲያኒቱን ደስ ሲላት በማየታቸው እንዲህ የሚል ቅኔ ቀኝተዋል ።

"ገብረ መንፈስ ቅዱስ ባዕል በበፍኖቱ
ወሰማዕት እንግዳ በቤቱ" ብለዋል ።

ይኸውም ቤተ መቅደስ (ቤተ መርቆሬዎስ) ከአስሩ አብያተ ክርስቲያናት አንደኛው ሲሆን በገነት አምሣል የተሠራ ስለሆነ የአለቃው ስም መልአከ ገነት ይባላል።

የዜናው አቅራቢ
አባ ዘካርያስ ዋሴ
ከ· ቅዱስ ላሊበላ

---

ድርብ ይሆናል ። ይህን የመሰለ በዓል ማክበር የክርስቲያን ደንብ ስለሆነ በዚህ ዕለት ምንም የሌላቸው ድሆች ወገኖቻችን ወስደን ካዘጋጀነው ምሳ ማሳተፍ ይገባናል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳ በምታደርግበት ጊዜ ችግረኞችን ጦም አዳሪዎችን ጥራ ይላልና በዓሉን በደስታ አክብረን ክብሩን ለመውረስ ያብቃን።

አባ ገብረ መስቀል ተስፋዬ
ዘገነተ ማርያም

---

# ቅንዓት

## ቅንዓት በሁለት ይከፈላል

፩. ሰይጣናዊ ቅንአት ፤
፪. መንፈሳዊ ቅንዓት ናቸው ።

ሀ/ ቅንአት ሰይጣናዊ ፤

ቅንአት ሰይጣናዊ በሌላው ሰው ሀብትና ጸጋ ችሎታ ወዘተ ሁሉ መቅናት እንዲሁም ለራሱ መመኘት ማለት ነው ። ስለ ቅንአት ሰይጣናዊ አጀማመርና መነሻነት ስናትት የአዳምንና የሔዋንን፤ እንደዚሁም የአቤልንና የቃኤልን አጭር ታሪክ ተገንዝበናል። ይሁን እንጂ ዲያብሎስ የቅንአት አመንጭና መሥራች እንደመሆኑ መጠን አሁንም ክፉ ሥራውን ሳይፈታ የቅንአተ ሥራውን በኋለኛው ትውልድ ሲያዘምት እናገኘዋለን ለምሳሌ ያህል በብሉይ ኪዳን ዘመን የተደረገውን የዮሴፍ ታሪክ ስንመለከት ወንድሞቹ ቀንተው በሽብር እንደሸጡት ቅዱስ መጽሐፍ ይገልጥልናል ። ዮሴፍ አባቱ ያዕቆብ እንደኛ ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ በጣም ስለወደደው ፤ ሁለተኛ ዮሴፍ በኋላ ዘመን ከሁሉ በላይ እንደሚሆንና በክብር ከወንድሞቹ እንደሚበልጥ በሕልም ስለተገለጠለት፤ ወንድሞቹ ሳይጠላቸው ጠሉት ፤ ሳይበድላቸው በደሉት በ፳ ብርም ለባዕድ ሀገር ሸጡት (ዘፍ.፴፯፡፬፡፳፰) የያዕቆብ ልጆች ወንድማቸውን እንዲሁ ከመሬት ተነሥተው በቅናት እስከ መሸጥ ያደረሳቸው ሰይጣናዊ ቅናት መሆኑን እንገነዘባለን። በተጠቀሰው ምዕራፍና ቁጥር እንደተገለጠው ሁሉ የያዕቆብ ልጆች አልሆን ብሎአቸው ነው እንጂ (እርስ በርሳቸው በሐሳብ በመለያየት) ወንድማቸውን ሊገድሉት ከፍ ያለ ፍላጎትና ጉጉት ነበራቸው ውስጥ ግን በእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ እንደዳነ ለመረዳት ይቻላል ። ከዚህም ሌላ በብሉይ ኪዳን ሕግ መሠረት አንድ ሰው ሚስቱን ታድርገው አታድርገውም በዝሙት ኃጢአት ቢጠረጥራትና ከዚህም የተነሣ ቅናት ሰይጣናዊ ቢያድርበትም እንኳ ሚስቱን ለካህን ያስመረምራት እንደነበረና ስለ ቅናቱም ሆነ ስለሚስቱ በኃጢአት መጠርጠር ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያቀርብ እንደነበረ በቅዱስ መጽሐፍ ተመዝግቦ አል (ኩኑልቍ ቍ.፭.፲፩-፲፭)

የሰይጣን ፍንጣሪ የሆነው ቅንአት ቀናተኛውን ሰው ከእሳት ውስጥ እንደገባ ገለባ ሲያቃጥለው እንደሚኖር ጥበበኛው ሰሎሞን ገልጦልን እናገኘዋለን ። ቅናት ሌላውን ሳይሆን በቅርብ በሥጋውም ሆነ በነፍሱ የምትጐዳው ቀናተኛውን ነውና (ምሳሌ ፲. ፴፬)።

በፍጹም ሕግ በሐዲስ ኪዳንም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጅን በነፍሱም ሆነ በሥጋው የሚያረክሰው የእርኵሰት ኃጣውዕ ሁሉ መነሻና ምንጭ የሆነው ቅንአት መሆኑን ቅዱስ ማርቆስ በጻፈልን ገልጦልናል ። (ማር.፯.፳፪) ።

ይህን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል በመከተልና የሕዝቡን ሕይወት በመመልከት የዘወትር ሐዋርያችን ቅዱስ ጳውሎስም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ልንከተለው የምንችልበትን እሱንም መስለን የምንኖርበትን ነገር ሲዘረዝርልን.... በዘፈንና በስካር አይሁን ፤ በዝሙትና በመዳራት አ ሁን ብሎ ከዘረዘረ

www.ethiopianorthodox.org

ሲገልጥ በክርክርና በቅንዓት አይ
ሁን” በማለት ነገሩን ሁሉ ደመደ
መው (ሮሜ ፲፫፡፲፫)
እንግዲህ እስከዚህ ድረስ በቅ
ናት ሰይጣናዊ ተነሣሥተው ወን
ድማቸውን የገደሉትን ፣ ሌሎችም
ወንድማቸውን ለገንዘብ በመለ
ወጥ ወንድማቸውን እስከ መሸጥ
የደረሱትን ወይም የሸጡትን አይ
ተናል ፣ ልንገነዘብም ችለናል ።
ስለዚህ ባየነው መሠረት በአሁኑ
ጊዜያችንስ በቅናት ወንድማቸ
ውን የሚገድሉ በቅናት በቀጥታ
ባይሆንም በተዘዋዋሪ መንገድ
ወንድማቸውን ለገንዘብ የሚለ
ውጡ የሉም ለማለት ይቻላልን?
የቅናት ሰይጣናዊ ፍሬና ውጤት
ባጭሩ ይህን የመሰለ ሲሆን በጠቅ
ላላ የቅናት ሰይጣናዊ ሁኔታን
በሌላው ርእስ እስክናመጣው
ድረስ ወደ ሁለተኛው እናመራ
ለን።

ለ.<u>ቅንአት መንፈሳዊ ፣</u>

ቅንዓት መንፈሳዊ ማለት ቃሉ
እንደሚገልጠው ሁሉ መልካሙ
ንና መንፈሳዊውን ሥራ ለመሥ
ራት መገፋፋትና መነሣሣት እንደ
ዚሁም ሌላው መልካምን ፣ መንፈ
ሳዊን ሥራ ሲሠራ አይቶ ሰው
ሳይጐዳ ሳይመቀኝ እንደዚያ ላድ
ርግ ልሥራ ማለትንና መሥራት
ንም ያጠቃልላል ።

መንፈሳዊ ቅናት የትሩፋት
ሁሉ ምንጭ እንደመሆኑ ውስጡ
ፍቅር ፣ ቅንነት ፣ እኩልነት ፣
ያለው ትሩፋት መሆኑን እንረዳ
ለን ፤ ቅናት መንፈሳዊ ያደረበት
ሰው መልካምን ለመሥራት ቀን
ከሌሊት ያለዕረፍት በመንፈስ
ቅዱስ ሲቃጠል ይኖራል ። ስለ
ዚህ ነው ጠቢቡ ሰሎሞን በመጽ
ሐፉ የቅንዓት መንፈሳዊን ነገር
[illegible] ቢገለጥ “የፍቅር ቅን
ዓት እንደ ሲኦል የጨከነች የጸ
ናች ናት… እንደ እግዚአብሔርም
ነበልባል ናት” በማለት የገለጠ
ልን (መኃልይ.፰.፮)

ቅንዓት መንፈሳዊ ያደረበት
ሰው በዚህ ብቻ አይወሰንም ፡
ከመልካም ሥራዎች አንዱ የእግ
ዚአብሔርን ስም መቀደስና በከን
ቱም እንዳይነሣ መጠበቅ ነው ።
ስለዚህ መንፈሳዊ ቅናት ያለውም
ሰው የእግዚአብሔር ክብር ፣ የእግ
ዚአብሔር ቅድስናና አምልኮት የባ
ህርዩ ላልሆነ ሥነ ፍጥርት ሲሰጥ
ባየ ቁጥር እንደእሳት ይቃጠላል ።
ለምሳሌ እውነተኛው ነቢይ ኤል
ያስ ሰዎች አማልክት ያልሆኑትን
አማልክት ናቸው በማለት የሐ
ሰት ትምህርታቸውን በማስራ
ጩት ብዙ ሕዝብ በኃጢአትና
በአምልኮ ባዕድ ባሳሳቱት ጊዜ
በንጉሥ በአክዓብ ፊት ሳይፈራ ፡
ሳያፍር ስለእግዚአብሔር አምልኮ
ቀንቶ ነቢያተ ሐሰትን “እስከ
መቼ ድረስ በሁለት አሳብ ታነክሳ
ላችሁ እግዚአብሔር አምላክ
ቢሆን እርሱን ተከተሉ በኣል ግን
አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ”
በማለት ሲዘልፋችውና ሲገስጻ
ቸው ፣ ብሎም ጣዖታቸውን በአም
ልኮተ እግዚአብሔር ውድቅ ካደ
ረገባቸው በኋላ በሰይፍ እንዳስገደለ
ቸው እንመለከታለን (ነገ.፲፰.፳)
፴፱፡፬፡፲ንና በጠቅላላ ምዕራፎቹን
መመልከት እጅግ ያስረዳናል።
ስለ እግዚአብሔር አምልኮና
ክብር ብቻም ሳይሆን ስለተቀደሰ
ቦታውም ወይም ቤቱም (ቤተ
መቅደስ) መንፈሳዊ ቅናት መቅ
ናት ለምእመን እንደሚገባ
ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ የቤትህ
ቅንዓት በልታኛለችና የሚሰድቡ
ህም ስድብ በላዬ ወድቆአልና
ሲል ስሙን በሚሰድቡና በሚያቃ
ልሉ ላይ በመንፈሳዊ ቅናት መነ
ሣት እንደሚገባ አስረድቷል
(መዝ.፷፰.፱) ይህ መንፈሳዊ
ቅናት ይልቁንም የትሩፋት ሁሉ
መሠረትና ጉልላት እንደመሆኑ
መጠን በሐዲስ ኪዳንም በሰፊው
ተገልጦልን እናገኘዋለን ። ለዚ
ህም የቅርብ ማስረጃ አድርገን
ልናቀርበው የምንፈልገው ፣ የም
ክራችንና የተገሣጻችን መዝገብ
የሆነው ሐዋርያችን ቅዱስ ጳው
ሎስ ሲሆን መንፈሳዊ ጸጋን ለም
ታስጠው መንፈሳዊ ቅናት እን
ዲት መነሣሣት እንዳለብን”
ቅንዑ ለእንተ ተዓቢ ጸጋ ለምትበ
ልጥ ጸጋ ቅኑ (መንፈሳዊ ቅናት
ይደርባችሁ ወይም ፈልጓት (ሲል
አስተምሮናል) ፩ቆሮ ፲፪፡፴፩ ።

ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ቤተ ክርስ
ቲያን ያለውን መንፈሳዊ ቅናት
ሲገልጥ “በእግዚአብሔር ቅን
ዓት እቀናላችኋለሁና በማለት ለቆ
ሮንቶስ ምእመናን ገልጦላቸዋል
(፪ቆሮ ፲፩፡፪) ።

ይህን መንፈሳዊ ቅናት ስናነሣ
ከዚህ ጋር አብሮ መነሣት የሚገባ
ውና ልንገነዘበውም የሚገባን ፡
እንደዚሁም በየጊዜው ከብዙ
ሰዎች ጥያቄን ሲያስከትል የሚኖ
ር ነገር አለ ። ይኸውም በብዙ
ቦታ እግዚአብሔር ቀናተኛ ነው
በሚል ቅጽል ተጠቅሶ መገኘቱ
ነው ። አዎን ይህ ቃል (ቀናተኛ
የሚለው) ለእግዚአብሔር ሲቀ
ጸል በምናገኝበት ጊዜ አእምሮአ
ችንን ወደ ሌላ አስተሳሰብ ሳይወ
ስድብን አይቀርም ይሆናል ብዬ
እገምታለሁኝ ። ስለዚህ መንፈ
ሳዊ ቅናት መሆኑን እንገንዘብ
ዘንድ ከዚህ ጋር አብሮ መግለጡ
መልካም ሳይሆን አይቀርም ።



እግዚአብሔር አምላክ በአምል
ኮቱ በቅዱስ ስሙ በክብሩ በባሕ
ርዩ የሚገባበትን ሰው ወይም ሌላ
ፍጡር (መልእክት) ዝም ብሎ
የማያይና እውነተኛ ፍርዱን የሚ
ፈርድ እውነተኛ አምላክ ነው
ስለሆነም እግዚአብሔር “እኔ ቀና
ተኛ ነኝ” ሲል ክብሬን ፣ አምልኮ
ቴን የባህርያቸው ላልሆነ ለባዕዳን
አማልክትና ለሥነ ፍጥረት ሲሰ
ጡብኝ ለምን ብዬ የምፈርድና
የምቆጣ ነኝ ማለቱ ነው ። እንጂ
ቀናተኛ ነኝ ምቀኛ ነኝ ማለቱ
አይደለም ። ይህን ቃል በመከተል
ከአምልኮ እግዚአብሔር ከሃይማ
ኖት ውጭ የሆኑ ሰዎችና ልባቸው
ቀረባ ቅርብ የሆኑ ሰዎች እግዚአ
ብሔር ለምን እንዲህ ይላል ፡
ለምንስ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጻፈ
የሚለውን ጥቃቅን የሆነ ጥያቄ
ሳያቀርቡ አይቀሩም ስለዚህ
ቅናት መንፈሳዊ የእግዚአብሔ
ርና የምእመናን ተቀዳሚ ተግባር
መሆኑን ተገንዝበው እሱን እንዲ
ከተሉትና ወደ ሃይማኖታቸው
መለስ እንደሚሉ ከፍ ያለ ተስፋ
አለኝ ።

እግዚአብሔር አምላክ የሰው
ልጅ ከአምልኮቱ ወጥቶ ሌሎች
ፍጡራን አማልክትን ሲከተል
እያየ ዝም ብሎ የማያይና እውነ
ተኛ ፍርዱን የሚይፈርድ ቢሆን
ኑሮ እውነተኛነቱ ቅን ፈራጅነቱ
ሁሉ በምናመልከውና በምንገዛ
ለት ምእመናን ዘንድ ግልጥ ሆኖ
ባልታወቀም ነበር ።

ስለዚህ የባሕርይ ክብሩን ፡
አምላክነቱን ቅዱስነቱንና የሱ
የሆነውን ሁሉ ለሥነ ፍጥረት
ሲሰጡበት ቀናተኛ ነኝ ማለቱ
ስለባሕርይ ክብሬ ፣ ስለአምላክ
ነቴ፣ ስለቅድስናዬ ፣ ቀንቼ እውነ
ተኛ ፍርዴን የምፈርድ እውነተኛ
አምላክ ነኝ ማለቱ መሆኑን ለሁላ
ችንም ቢሆን ግልጥ ሊሆን ይገ
ባል ። የቀደሙ አባቶች ይህንን
ምሥጢር በተረት መልክ ሲገ
ልጡ “አምላክ በአምልኮቱ ፣ ባለ
አባት በርስቱ ጐልማሳ በሚስቱ
ቀናተኛ ነውና ይላሉ ይህም ማለ
ታቸው ዝም ብሎ አይደለም የተቻ
ለውን ያህል የልቡን ፍርድ ይፈር
ዳል ፣ እንዲያውም ዝም ሊል
አያስችለውም ማለታቸው መሆኑ
ግልጥ ነው ። ከዚህ ቀጥለን ይህን
ቃል ቀናተኛ የሚለውን የሚገል
ጡልንን ጥቅሶች እንመለከታቸዋ
ለን እነሱም ፣

ዘጸ. ፳፡፭
”. ፴፬፡፲፬
ዘዳግ. ፬.፳፬
”. ፭.፱
”. ፮.፲፭
ኢ.ያሱ ፳፬፡፲፱
መዝ. ፸፯፡፸፰/፶፰
መዝሙር ፸፱፡፱
ሕዝቅ. ፴፱፡፳፭
”. ፴፮.፭
ናሆም ፩.፪
መዝ. ፸፰.፭ ወዘተ ናቸው
ኢዩኤ. ፪፡፲፰ ፣
ዝክ. ፩፡፲፬
” ፰፡፰ ናቸው ።

ለምሳሌ ያህል ጐልተው የሚ
ታዩትንና በቅርብ የሚገኙትን እነ
ዚህን ጠቀስን እንጂ ይህ ቃል
እውነተኛ ዶግማ (ነገረ እግዚአብ
ሔር) እንደመሆኑ የማይጠቀስ
በት ከቅዱስ መጽሐፍ ክፍል አነስ
ተኛ ነው ቢባል ማጋነን አይሆ
ንም ።

የቅናት መንፈሳዊ ይዞታውም
ሆነ አገላለጡ ይህን ይመስላል ።
በዚህ በቅናት መንፈሳዊ ብዙ
መንፈሳዊ ዓላማና መመሪያ እንደ
ተመለከትን ይታመናል ። ስለሆ
ነም ጌታ እግዚአብሔር ለአምል
ኮቱ ፣ እነ ኤልያስ ፣ እነጳውሎስ
ወዘተ የመሳሰሉት ምእመናንም
ለእግዚአብሔር አምልኮት ያላቸ
ውን መንፈሳዊ ቅናት ሲገነዘቡ
እኛስ? የሚለው መንፈሳዊ ጥያ
ቄን ራሱ አእምሮአችን እኛን ሳይ
ጠይቀን አያልፍም ታዲያ መል
ሱስ ምን የሚል ይሆን? እውነትን
የተከተለ ፡ ሐቅን ያዘለ ቅናትስ
በዓለም ይኖራልን? መልሱን ለአ
እምሮአችን ፍርዱንም ለእግዚአ
ብሔር እንተወው ። ከዚህ ቀጥለን
የቅናት ጠቅላላ መግለጫውንና
ማጠቃለያውን እናያለን ።

<u>ጠቅላላ መግለጫውና ማጠቃ
ለያው ፡</u>

እስከ አሁን የቅናትን አጭር
ዝርዝርና ይዞታ ተመልክተናል ።
ከዚህ አያይዘን ደግሞ አጠር ያለ
(ማብራሪያውንና) ማጠቃለያውን
እንመለከታለን ።

ክርስቲያኖች ሆይ! ከመጀመ
ሪያ ጀምሮ እንደተገለጠው ሁሉ
ቅዱሳት መጽሐፍት በየምዕራፋ
ቸው በየአንዳንዳቸው ሁሉ እንደ
ሚገልጡት ሰይጣናዊ (ሥጋዊ)
ቅናት ያለበት ሰው እግዚአብሔ
ርን አምናለሁኝ ብሎም ክርስቲ
ያን ነኝ በማለት እንኳንስ ለመና
ገር ቀርቶ በልቡ ለማሰብም አያስ
ደፍረውም ።

የቀናተኛ ምቀኛ ሰው ዓላማና
መጥፎ እርምጃው እንዲያው ተነ
ግሮ አያልቅም ይሁን እና እስቲ
መለስ ብለን ቃኘት እናድርገው ።

በየክፍሉ እንደተገለጠው ቀና
ተኛ (ምቀኛ) ሰው የዲያብሎስ
እንደራሴ ነው እንዲያውም ግዙፉ
ዲያብሎስ ነው ቢባል ማጋነን
አይሆንም ዲያብሎስ ከጥንት
ጀምሮ የቅናት መርዙን የሚረ
ጨው በርቀት ሳይታይ ሳይገለጥ



www.ethiopianorthodox.org

# የማይሞተው አምላክ

የማይሞተው አምላክ የሰላም ባለቤት
እንደ ኃላፊ ሰው እንደተራ ፍጥረት
ቁጣን ተቀበለ ቀረበ በሰው ፊት
መስጠትና መንሣት መግደልና ማዳን
የሚቻለው አምላክ ተቀበለ ፍዳን
የሰላም ባለቤት የአማልክት ጌታ
እንደ ወንጀለኛ በጥፊ ተመታ
አወይ የሰው ነገር ሀሳቡ ጠማማ
ቸሩ ፈጣሪውን ሊሸጠው ተስማማ
ልቅሶ ይገባዋል ወዮለት ይሁዳ
ስለተጻፈበት የማይፋቅ ፍዳ
ስግብግብ ነጋዴ ግፍን የማይረሳ
መድኃኔ ዓለምን ሸጠው በሰላሳ
ይሁዳ የሚሉት ተንኮለኛው ሰው
ሊሸጠው ሲፈልግ በግፍ ሊያሲዘው
በተንኮል ተሞልቶ ሮጦ ሳመው
የሳምኩት እርሱ ነው ያዙት አላቸው
ወዮ ፈጣሪያችን የምህረት ባለቤት
ተሰብስበው ያዙት ሁሉም ዘበቁበት
ይዘው እያዳፉ ከመሬት ጐተቱት
ሰማይና ምድርን በቃሉ ያዘዘ
ወዮ ፈጣሪያችን በጠላት ተያዘ
ምን ዓይነት እጅ ነው ምንስ እንደበት
መቆጣት የሚችል ወይም መማታት
የሰላሙ[illegible]ላክ የፈጣሪን ፊት
እ[illegible] አቤት ትዕግሥት
መ[illegible] ማጥፋት
በሎሌዎቹ እጅ ትገርፎ መሞት
በጣሙን ዕፁብ ነው ድንቅ ነው ሰውነት
ይዘውም አቆመው በጲላጦስ ፊት
የሃሰት ምስክር ገዝተው ከሰሱት
የሐሰት ምስክር በገንዘብ ተገዝቶ
አሳልፎ ሰጠው ፈጣሪውን ክዶቶ
የኃያላን አምላክ የነገሥታት ንጉሥ
በጥፊ ተመታ ኢየሱስ ክርስቶስ
ጲላጦስ ገረፈው ደግሞም ጐተተው
አዘውታልና ግረፈው ብለው
አይሁድ ተሰብስበው አበዙ ጩኸት
ስቀለው እያሉ ሁሉም በአንድነት
የፊጥኝ አሰሩት ሸፍነው ፊቱን
ያሰቃዩት ጀመር ፈጣሪያችንን
ማን መታህ ተናገር ተነበይ እያሉ
እየተሳሳቁ ዘበቱበት ሁሉ
ከብርሃናት ይልቅ የሚያበራው ፊት
እይተውት ያልቆሙ አሪትና ነቢያት
ምራቅ ተተፋበት በሐሰት ካህናት
ወዮ ፈጣሪያችን አምላክ ምህረት
ለአገዛዙ ወሰን ለሰላሙ ልክ
እንከን የሌለው መሃሪው አምላክ
በአደባባይ ዋለ ደፍቶ የአክሊል ሶክ
ሰማያት በቃሉ የሚታዘዙለት
ምድርም ትዕዛዛቱን የምትጠብቅለት
ሱራፌል መንበሩን የሚሸከሙለት
ደግሞም በመንቀጥቀጥ የሚያመሰግኑት
ወዮ ፈጣሪያችን ምራቅ ተተፋበት
ለኛ ስትል ግፍን ስቃይን ተቀብለህ
አይሁድ ዘመቱብህ ከልብስ አራቆቱህ
ክርቤንም ከሃሞት ቀላቅለው አጠጡህ
ጥመኞችን ሁሉ የሚያረካው ጌታ
ተጠማሁ በማለት ደከመ ላንዳፍታ
ኃያሉ ፈጣሪ አካላዊው ቃል
ወዮ ተሰቀለ በሽፍቶች መሃል
ሉዓላዊው አምላክ ተሰቅሎ ብታይ
ፊቱቿን ሸፈነች ወ ሮ ዐሐይ
ደግሞም ተሸሸጉ ከመሬት በታች
ከዋክብተ ሰማይ የዐሐይ ልጆች
ከሲዖል ለማዳን የኃጥአንን ነፍስ
ይኸው ተሰቀለ ሕያው ክርስቶስ
እስኪ እኛም እናልቅስ እንባ እንኳ
እናፍስ
ጨረቃ እንኳ በአቅሟ ደምን ስታለቅስ
በመስቀል ላይ ሲውል አምላክ ሰላም
ሲዖል አለቀሰች ታወከች በጣም
በአካለ ነፍስ ወደ ሲዖል ወርዶ
ባዶዋን አስቀራት ለአዳም ልጆች ፈርዶ
ፈጣሪ በሲዖል ነጐድጓድ ሲያሰማ
ሲመላለስባት በሚያስፈራ ግርማ
ሲዖል ደነገጠች ወደቀች ተዳከማ
ሰውን በመውደዱ ፍቅሩን የገለጠ
ክርስቶስ ብቻ ነው ሕይወቱን የሰጠ
የአዳም ቃል ኪዳን እየገሰገሠ
ፈጣሪውን ይዞ ዓርብ ቀን ደረሰ
አንች ቀራንዮ ምንኛ ታደልሽ
የፈጣሪ ደሙ የፈሰሰብሽ
የእስራኤል አምላክ የሰላሙ ጌታ
እኛኑ ለማዳን ሲወድቅ ሲንገላታ
ምን ይሆን ወገኖች የሰዎች ውለታ
ልባችን እናቅና እንዲሆን አስፋልት
በኮሮኮንች መሄድ አይችልም ጸሎት
ዳግመኛም ይደልደል እንዳይሆን
እንጋዳ
ዘንቶ እንዲመላለስ የጸሎት እንግዳ
እንደኛ እንኳ ሳይሆን እንደበደላችን
እንደቸርነትህ ማረን ፈጣሪያችን ።
አዘጋጅ፣ ደቀ መዝሙር መልአኩ አስማማው
ከዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ የመምህራንና ቀሳውስት ማሰልጠኛ መ/ት/ቤት

---

በሥውር ነው ቅናት (ምቀኛ) ሰውነትን የቅናት መርዙን ሲረጭም ሆን ሲጐዳ እየታየ ፣ በገዙፍ ተገልጦ ነውና ።

ከዚህም ሌላ ቀናተኛ ሰው ከእግዚአብሔር መንግሥትና ከማኅበራዊ ኑሮ ሕግ የወጣ እንቢተኛ ነው ። ስለሆነም የእግዚአብሔርን መንግሥት በኋለኛውም በአሁኑም ዘመን ሊወርስ ሊያይ እንደማይችል ቅ/ጳውሎስ ገልጦልን እናገኛለን (ገላ.፭.፳)

ከመ/ዘርአ ዳዊት አድኃና

# በፍቅራችን መካከል ግብዝነት አይኑር

[illegible]ዛዛቱ ሁሉ መደምደሚ የወ[illegible]ቅር ነው ነገር ግን መንገዱ አንድ አይደለም የተለያዩ ብዙ መንገዶች አሉት ፣ በሥጋ ወልደው በወተትና በፍትፍት አሳድገው ለቁም ነገር የሚያበቁ ወላጆች ይወደዳሉ ፣ ከሕፃንነት ጀምረው አፈር እየተራጩ ውሀ እየተጐናጩ በአንድ ላይ ያደጉ ጓደኛዎችም ይፋቀራሉ ፣ እንዲሁም አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት ይብቃ ተብሎ በታዘዘው መሠረት በሥነ ሥርዓት ተጋብተው እየተረዳዱ የሚኖሩ ባልና ሚስትም ይፋቀራሉ ከዚህም ሌላ ልጆች ወላጆቻቸውን ወላጆች ልጆቻቸውን ያፈቅራሉ ሌላም ይህንን የመሰለ ፍቅር ያለ በመሆኑ የፍቅርን ዘርፍ ጨርሶ ለመጻፍ ያዳግታል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደኛ ሰው ሆኖ ሥጋን ለብሶ በዚህ ዓለም እየተመላለሰ ያስተምርበት በነበረው ጊዜ ሕገ ኦሪትን ጠንቅቄ አውቃለሁ ፣ እጠብቃለሁ የሚል አንድ ሰው ሊፈትነው ፈልጎ ወደ እርሱ ቀረበና መምህር ሆይ ። ከሁሉም የሚበልጥ ትእዛዝ የትኛው ነው ። ሲል ጠየቀው ጌታችንም ጥያቄውን ተቀብሎ የሰጠው መልስ “እግዚአብሔር አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹም አሳብህ ውደድ ከሁሉ የሚበልጠውና የመጀመሪያው ትእዛዝ ይህ ነው ካለ በኋላ ከዚሁ በመቀጠል ይህንንም የሚመስለው ሁለተኛው ትእዛዝ ሰውን ሁሉ እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ የሚለው ነው የሙሴ ሕግና የነቢያት ትምህርት ሁሉ የተመሠረቱትም በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ላይ ነው አለው ማቴ ፳፪ ፴፬—፵

ሐዋርያው ጳውሎስም ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ እምነት ተስፋ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ ፣ ነገር ግን ከእነዚህ መካከል ብልጫ ያለው ፍቅር ነው እንግዲህ ከሁሉ ይበልጥ ፍቅርን ተከታተሉ ብሏል ፩ኛ ቆሮ ፲፫ ፲፫ ፲፬ ፩

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ እንደሰው እየተራበ እየተጠማ ከኃጢአት በስተቀር በሰው ላይ የሚደርሱትን ችግሮች ሁሉ እየተቀበለ አድጎ በሠላሳ ዘመኑ ተጠምቆ የዕዳ ደብዳቤያችን በጥምቀቱ ደምስሶ ወደገዳመ ቆሮንቶስ ገብቶ በመጾምና በመጸለይ በተለያዩ መንገዶች የመጣውን ሰይጣን ድል ነሥቶ ደቀመዛሙርቱን መርጦ ሦስት ዓመት ከሦስት ወራት አስተምሮ ሲያበቃ በመልዕልተ መስቀል ላይ ተሰቅሎ ሙቶ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ የሰውን ልጅ ከፍዳና ከመርገም ነፃ ያደረገው ሰውን ከመውደዱ የተነሣ ነው ፣ ይህንንም በዮሐንስ ወንጌል ሲገልጽ እግዚአብሔር ዓለሙን ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው ልጁን እስከ መስጠት ደርሶ ወዶታልና ብሏል “ጠላቶቹ ስን ሆን በልጁ ሞት ይቅር አለን ሲል ሐዋርያው ጳውሎስም ተናግሯል።

ፍቅር ማለት የሚወደውን መውደድ ሳይሆን የሚጠላውን መውደድ ነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደተባለ ሰምታችኋል ፣ እኔ ግን እላችኋለሁ በሰማያት ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሟችሁንም መርቁ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ ብሏል ማቴ ፭ ፵፫

ሐዋርያው ጴጥሮስ ለእውነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት በሌለበት በወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ ይላል ፩ኛ ጴጥ. ፪ ፪

ሐዋርያው ዮሐንስ ደግሞ ዓለሙን ወይም በዓለም ያለውን ሁሉ አትውደዱ በዓለም ያለው ሁሉ የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለገንዘብም መመካት ከዓለም ነው እንጂ ከእግዚአብሔር ስላልሆነ ማንም ዓለምን ቢወድ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም ዓለሙም ምኞቱም ያልፋል የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘለዓለም ይኖራል ይላል ፩ኛ ዮሐ ፪ ፲፭

በሌላም በኩል ሐዋርያው እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ መንድሙን ቢጠላ ሐሠተኛ ነው ያየውን ወንድሙን የማይወድ ከሆነ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወድ ይችላል ? እግዚአብሔርን የሚወድ መንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን ይላል ፩ኛ ዮሐ ፬ ፲፰

ለደስታም ሆነ ለመከራ ለጥጋብም ሆነ ለረኀብ ለድኅነትም ሆነ ለብልጽግና ፍቅር ከፍተኛ መሣሪያ ነው ሥራ ተሠርቶ ጥሩ ውጤት ሊኖረው የሚችለው በፍቅር አብሮ የተሠራ እንደሆነ ነው በእግር የሚጓዙ መንገደኞች እጅግ በጣም የራቀውን መንገድ ሳይታወቃቸው አቋርጠው ካሰቡት ለመድረስ የሚችሉት በፍቅር አብረው የተጓዙ እንደሆነ ነው ፣ ኑሮም ጣዕምና ለዛ የሚኖረው በፍቅር የተያዘ እንደሆነ ነው፣ ለምሳሌ ቅመማ ቅመሞች ተሰብስበው ጨው ካልተጨመረባቸው ጣዕም ሊኖራቸው እንደማይችል የዚህ ዓለም ጉዳይም ፍቅር ከጐደለው ዋጋ የለውም ።

ፍቅርም ሲባል ከልብ እንጂ ከአንገት በላይ ለይስሙላ መሆን የለበትም በገንዘብና በልዩ ልዩ ጥቅምም መለወጥ አይገባውም አንድ ታሪክ ቀጥለን እንመልከት እጅግ የሚፋቀሩ ሁለት ጓደኛሞች ነበሩ የሚኖሩት በአንድ ቤት ሆኖ ሥራቸው የተለያየ ነበር አንደኛው ቀድሞ ከቤት የደረሰ እንደሆነ ወንድሜን ምን አገኘው በማለት ከቤቱ ውጭ ሆኖ ይጠብቀዋል እንጂ ወደቤቱ አይገባም ነበር ። ከዕለታት አንድ ቀን አብረው መንገድ ሲሄዱ ድስት ሙሉ ወርቅ አገኙ ገንዘቡን ካገኙ በኋላ ፍቅራቸው እየቀዘቀዘ ይሄድ ጀመር እጅግ ይነፋፈቁ የነበሩ ፍቅሩ ቀረና አንደኛው ወንድሜ ሙቶልኝ ወርቁን ብቻየን ወስጄ





www.ethiopianorthodox.org

ቢል ሌላውም በበኩሉ ይህንን ክፉ አሳብ ከልቡ ያወጣና ያወርድ ጀመር ከዚህ መካከል አንደኛውን ኮሶ ታየው ፡ በዚህ ጊዜ እንግዲህ ወንድሜን ኮሶ አጠጣኝ ብዬ ሊያጠጣኝ ሲል አንሥተህ ስጠኝ እለዋለሁ አንስቶ እሰጣለሁ ሲል በሰይፍ አንገቱን ብየ ገድየ ኮሶየን በመጠጣት ከበሽታዬ ተገላግዬ ወርቄንም ለብቻየ እወስዳለሁ ብሎ አሰበ ሌላውም በበኩሉ ወንድሜ ኮሶ አጠጣኝ ብሎ ጠይቆኛል ፤ ከኮሶው ጋር የሚገድል መርዝ ቀላቅየ አዘጋጅቼ ያነን ጠጥቶ ሲሞትልኝ ወርቄን እወስዳለሁ ብሎ አሰበ ።

በዚህ መሠረት አንደኛው ኮሶውን ከመርዝ ጋር አዘጋጅቶ ና አዘጋጅቼልሃለሁ ጠጣ አለው መጥቶ አንሥተህ ስጠኝ አለው አንሥቶ ሊሰጠው ጐንበስ ሲል በሰይፍ አንገቱን በጥሶ ገደለውና ኮሶውን አንሥቶ ጠጣ መርዝ ተቀላቅሎበታልና ወዲያውኑ ፍግም ብሎ ሞተ ። ሁለቱም ስለሞቱ የሁለቱም የሳሱለት ወርቅ ለማንም ሳይሆን በሜዳ ቀረ ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት አንዱ ይሁዳም ተመርጦ ገንዘብ ጠባቂ ነበር ከሚገባውም ገንዘብ ከመቶ አሥር እንዲወስድ ጌታችን ፈቅዶለት ነበር ። አንዲት ሴት ፫፻ ብር የሚያወጣ ሽቱ አምጥታ ለጌታችን ለመድኃኒታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አስረከበች ይሁዳ ከመቶ አሥሩ ሳይከፈለው ስለ ቀረ በጣም ተናደደ በዚያ ወቅት አይሁድ ክርስቶስን ይዞ ለመስቀል የሚጥሩበት ጊዜ ነበር ክርስቶስን ጠቁሞ ለሚያስይዘን ገንዘብ እንከፍላለን እያሉ ይናገሩ ነበርና ይሁዳ ሰላሳ ብር ስጡኝና እኔ አሳያችኋለሁ ብሎ ብሩን ተቀብሎ ጭፍሮችን እየመራ ጌታችን ወደ አለበት ሄደ ወደ እርሱ ለመድረስ በተቃረበ ጊዜ ሰላም ለአንተ ይሁን ብዬ የምስመው ክርስቶስ ነውና ተረባርባችሁ እንድትይዙት ብሎ መከራቸው ሰላም ብሎ ጉልበቱን ለመሳም ለጥ ሲል ፍቅሩ የአንገት በላይ ሰላምታው አፍአዊ መሆኑን ጌታችን ስለሚያውቅ ይሁዳ በመሳም ልታስይዘኝ መጣህን አንተ በተንኮል ያስያዝኩት ይመስልሃል ፤ ነገር ግን እኔ ወደዚህ ዓለም የመጣሁት ፣ ተሰቅዬ ሙቼ ሰውን ከፍዳና ከመርገም ነፃ ለማውጣት ነው ። ብሎ ለመያዝ የመጡትን እንቅፋት እንዳይመታቸው እሾህ እንዳይወጋቸው ወደ አለበት ቀርቦ በፈቃዱ እጁን ሰጥቷል ።

አይሁድ ጌታን ይዘው የግርግሪት አሥረው እየጐተቱና እየደበደቡ ሲወስዱት ይሁዳ አይቶ ይህንን የተቀበለውን ፴ ብር ወስዶና እርሱን ተውልኝ ገንዘባችሁን እንኩ ውሰዱ አላቸው አይሁድም ለአንተ የፈለግኸውን ገንዘብ ሰጥተንሃል ፡ ለእኛም የምንሻውን ኢየሱስን አስይዘኸናል ። እንግዲህ ወዲህ አንተ ከእኛ እኛ ከአንተ ምን አለን ፡ ገንዘብህን አንቀበልም ከፈለግኸው ጣለው አሉት፡ ይሁዳም ያንን የ[illegible]ለትን ገንዘብ ከጠረጴዛው ላይ በተና ታንቆ ሙቷል ፡ የገንዘብ ፍቅር መጨረሻው ጥፋት ነው ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነው። አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን አጠፉ በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክቱ ገልጿል ፩ኛ ጢሞ ፮.፲

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረን መውደድ የሚገባን በአንደኛ ደረጃ እግዚአብሔር አምላካችን ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ወንድማችን ነው በእነዚህ ሁለት ትእዛዛት የቀሩት ትእዛዛት እንደሚጠቃለሉ ከላይ ተመልክተናል ።

ዓለሙንና በዓለሙ ያለውን አትውደዱት ሲባል ሁሉን እንጥላው እንቅረን እንትፋው ማለት አይደለም በዓለም ተቀምጠን ከዓለም ውጭ ልንሆን አንችልምና ነገር ግን ሁሉም በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሚፈጸም አምነን በፍቅር ተባብረን ሥራችን ማከናወን ይኖርብናል አግባብ የሌለው ፍቅር መቅሠፍትን እንደሚያስከትል መረዳት አለብን ፤ አብረን ስንኖር በኅብረት አብረን ሥን ሥራ መተማመንና መፋቀር እንጂ እርስ በእርሳችን መፈራራት የለብንም በፍቅራችንም ግብዝነት ሊኖርበት አይገባም ፍቅራችንም ከጸና፡ እርስ በእርሳችንም ከተዋደድን እግዚአብሔር ከእኛ አይለይም ። እግዚአብሔር ፍቅር ነው ተብሎ ተጽፏልና ።

ሊ. ኅ ልሣነ ወርቅ በዛብኅ



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የሰብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ። ለዚሁ ጥያቄ ቢሮርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋሪያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቍ·
የመልእክት ሣ·ቍ· 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org